# ምዕ. 13 መንፈሳዊ ውጊያ

ለሙስሊሞችም ሆነ ወይም በዚህ ዓለም ለሚገኙ ለሌሎችም ማናቸውም ሰዎች በሚመስለን መንገድ ሁሉ ለመመስከር ከመሰማራታችን በፊት፣ ይህን ርዕሰ ጉዳይ ልንረዳው ይገባል። የእግዚአብሔር ቃል በሰማያዊ ስፍራ ያለማቋረጥ ስለሚካሄደው መንፈሳዊ ጦርነት ደጋግሞ ይጠቅሳል። ይህም በአንድ ወገን በእግዚአብሔርና በቅዱስና መላእክቱ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በሰይጣን፣ በርኩሳን

መናፍስቱና አጋንንት መካከል የሚካሄደው የከፋ ግጭት ነው። «መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዢዎች ጋር በሰማያዊ ስፍራም ካሉ ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ» (ኤፌ. 6፡12)።

ጌታ ኢየሱስ ሰይጣንን በእነዚህ አስደንጋጭ ቃላት ይገልጸዋል፥ «እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ... ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና» (ዮሐ. 8፡44)። በሰው ልጅ ላይ አሰቃቂ ውጤቶችን ያስከተለው የአዳምና የሔዋን ዓመፅ በኤድን ገነት የተቀነባበረው በሰይጣን የማሳት ተግባር ነው። ከዚህም የተነሣ አሁን «... ዓለምም በሞላው በክፉው እንደ ተያዘ እናውቃለን» (1ኛ ዮሐ. 5፡19)። ስለዚህ የሚነሣው ጥያቄ ሰው መታዘዝ ያለበት ለእግዚአብሔር ነው ወይስ ለሰይጣን? የሚል ነው።

ለፍጥረቱ ካለው ታላቅ ፍቅር የተነሣ እኛን ወደ ራሱ ለመሣረክ፥ እግዚአብሔር ከጠላታችን ጋር ውጊያ ከፍቷል። «እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ (ኢየሱስ) ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፥ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ» (ዕብ. 2፡14፥ 15)።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር የኤልሳዕን ሎሌ ዓይኖች በመክፈት ከጠላት ትይዩ የተገጠገጡትን «የእሳት ሰረገሎች» ለማየት ቢያስችለውም፥ ዳሩ ግን በሰማያዊ ስፍራ የሚካሄደው ውጊያ ለሰብአዊ ዓይን የሚታይ አይደለም (2ኛ ነገ. 6፡17)። ታዲያ ይህ ፍልሚያ ቢታይም ባይታይም ውጊያው ግን እውነተኛና የሰውን ልጅ ሁሉ ያካተተ ነው።

ሰይጣንንና ሥራዎቹን ሁሉ ክደን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነት ሥር ስንጠለል አቋማችን ይቀየራል። በዚህ ጊዜ በግላችን የጦርነቱ ተሳታፊዎች እንሆናለን። ኤፌሶን 6፡10-18 እንዴት በውጊያው እንደምንሳተፍና እንደምንታጠቅ በዝርዝር ያስረዳናል።

> «በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ። የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካሉ ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ። እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥

የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤ የመዳንንም ራስ ቍር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ።»

## ሰይጣንን መቋቋም

አንድ ወታደር ለውጊያ በሚዘጋጅበት ወቅት በሁለት ሁኔታዎች ላይ ሥልጠና ማግኘት አለበት - በማጥቃት እና በመከላከል። በመንፈሳዊ ውጊያም ሁኔታው ተመሳሳይ ስለሆነ፥ አማኝ ሁለቱንም በተመለከተ በቅድሚያ ራሱን ማዘጋጀት አለበት። በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ማለፍ እንድንችል እግዚአብሔር ብርቱ የጦር ዕቃ እንዳዘጋጀልን ከላይ ከተጠቀሰው ክፍል እንመለከታለን። ይሁንና በዚሁ ጥቅስ ውስጥ ስለመከላከል የተለየ አትኩሮት የተደረገበት ይመስላል። «መቆም» የሚለው ቃል አራት ጊዜ ተጠቅሷል። ለአማኝ መቆም ማለት ምን ማለት ነው?

ልማዳዊው የእስልምና ሃይማኖት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ውስጥ በአስማታዊ ዘዴዎችና ጥበቦች ሲጠቀም ይታያል። እነዚህ ዘዴዎች ሰይጣን በርኩሳን መናፍስቱና በአጋንንቱ አማካኝነት ራሱን ለመግለጽና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመቃወም ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ነው። ጽኑ ፍርሃት በማሳደር ለመቋቋም ይሻል። ለዚህም ከጋና የተገኘ አንድ ምሳሌ አለ። ሙስሊሞች የቁርዓንን ክፍሎች በቃላቸው በሚሸመድዱበት ወቅት አጋንንት ክርስቲያንን እንዲገድሉ፥ ቤተሰቡን እንዲጐዱ ወይም ወደ ኃጢአት እንዲመሩት በመጣራት የሆነ ሥነ ሥርዓት ያካሂዳሉ። ይህም ልምምድ ፍጹም ስለሚታመንበት፥ «ከቶውንም ዝንፍ አይልም» በሚል አስተሳሰብ፥ «ሲሩ» ተብሎ ይታወቃል።

አንድ ክርስቲያን የእንደዚህ ዓይነቱ አስማታዊ ልምምዶች ዒላማ ከሆነ ምን ማድረግ አለበት? ይህ በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል የሚደረግ ፉክክር መሆኑን ማኅበረሰቡ ሁሉ የሚያውቀው ነው። ማንነው ታላቁ ኃይል? ማን ያሸንፍ ይሆን? ሁሉም ውጤቱን ለማየት ይጠባበቃል።

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ አማኝ በጽናት «እንዲቆም» ነው የታዘዘው። የኤፌሶንና የቈላስያስ መጻሕፍት በመጀመሪያ ምዕራፎቻቸው ጌታ ኢየሱስ «ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ ጉልበት ይታያል፤ ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት፤ ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ

ክርስቲያን ሰጠው። እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት» (ኤፌ. 1፡21-23) በማለት ፍጹም የከበረ መሆኑን ይመሰክራሉ። እነዚህ ምዕራፎች ክርስቲያን በእግዚአብሔር የጦር ዕቃ የተጠበቀ ነው። ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እርሱ በ«ክርስቶስ ውስጥ» ስለሆነና ክርስቶስም «በእርሱ ውስጥ» ስለሆነ የተጠበቀ መሆኑን ያስተምሩናል። የትኛውም ክፉ ኃይል ጌታ ኢየሱስን ሊረታ አይችልም፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ስለተከለልን ምንም ክፋት ሊጐዳን አይችልም። ስለዚህ አንድ ክርስቲያን የአስማት ድግምት እንደተነጣጠረበት ቢያውቅም ራሱን ያለ ምንም ማወላወልና ፍርሃት ለጌታ አሳልፎ መስጠት ይገባዋል። ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በውስጡ በሚኖረው የጌታ ኢየሱስ መከላከያ ኃይል በመተማመን የተለመደ ሕይወቱን መቀጠል ይገባዋል።

## በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሞላት

ለመንፈሳዊ ውጊያ ስለሚያስፈልጉን ጦር ዕቃዎች (መሣሪያዎች) በምንመለከትበት ጊዜ ሁለቱን በኤፌሶን መጽሐፍ ምዕራፍ 6 ላይ ተጠቅሰው እናገኛለን። እነርሱም «የመንፈስ ሰይፍ» የሆነው የእግዚአብሔር ቃል እና «ጸሎት» ናቸው። በዚህ መጽሐፍ ከዳር እስከ ዳር ድረስ ለማሳየት የሞከርኩት የእስልምናን እስራት ከሙስሊሞች ሕይወት ውስጥ ለመበጠስ፥ የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ መጠቀም የቱን ያህል እንደሚረዳን ነው። የሰይጣንን ውሸትና አታላይነት በእግዚአብሔር ቃል እንዋጋለን፥ «ቃልህ እውነት ነው» (ዮሐ. 17፡17)።

«ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ» የሚለው ሁለተኛው የማጥቂያ መሣሪያ ነው። ለአገልግሎት ኃይልን የሚሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው። ከትንሣኤው በኋላ ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» ብሎአቸዋል (ሐዋ. 1፡8)። ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ ስለ አገልግሎቱ «... በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል፥ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል ... የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬአለሁ» (ሮሜ 15፡19) በማለት ተናግሯል።

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማክበር እንደሆነ ማስተዋሉ አስፈላጊ ነው። «እርሱ ያከብረኛል፥ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና» (ዮሐ. 16፡14)። መንፈስ ቅዱስ ፈጽሞ የራሱን ክብር አይሻም፤ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስን ለማክበር ይሠራል።

# የክፉት ኃይል መገለጫዎች

በዚህ መጽሐፍ 10ኛ ምዕራፍ ላይ ስለ ምልጃ ጸሎት ማጤናችን ይታወሳል። አሁን ደግሞ እግዚአብሔር ጸሎታችንን በመመለስ፥ እንደምን በክፉ መናፍስት ላይ በገዛ ግዛታቸው ውስጥ የኃይሉ መግለጫ የሆነ እርምጃ እንደሚወስድባቸው እናጤናለን።

«ልማዳዊ» እስልምና በሚካሄድበት ስፍራ ብዙውን ጊዜ ክፉ ተግባራት ይታያሉ። መናፍስትን መጥራት ወይም የሙታንን መንፈስ መሳብ፥ ጥንቆላ፥ ማለትም መተት፥ በድግምት መፈወስ፥ ርግማን እና እንደ ክታብ ማሰር የመሳሰሉትና እንደዚሁም የወደፊቱንና የአሁኑን ሁኔታ ለመግለጽ የሚደረግ ኮከብ ቆጠራን ያጠቃልላል። ክርስቲያን ያልሆነው ዓለም ይህንን በመሳሰለው የርኩስ መንፈስ ኃይል መግለጫዎች ይመሰጣል፤ የሚከተላቸውም መንገዶች እነዚሁ ናቸው። ከዚህ ሁሉ ሥርዓት በስተጀርባ የክፉው የሰይጣን እጅ አለ።

እነዚህ ተግባራት እያንዳንዳቸው በእግዚአብሔር የተከለከሉ መሆናቸውን በደንብ ልብ በል። «... ምዋርተኛም፥ ሞራ ገላጭም፥ አስማተኛም፥ መተተኛም፥ በድግምት የሚጠነቍልም፥ መናፍስትንም የሚጠራ፥ ጠንቋይም፥ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ። ይህንንም የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው» (ዘዳ. 18፡10-12)። እነዚህ በጣም ከበድ ያሉ ቃላት ስለሆኑ አማኞች ይህንን ማስጠንቀቂያ በጽኑ ሊያከብሩት ይገባል። ባህልህን ተከትለህ እንደነዚህ ላሉ ተግባራት ቋሚ ዝንባሌ እንዳይኖርህ ተጠንቀቅ። አማኞች እንኳ እንዲህ ባለው የኃይል መግለጫ ሊማረኩ ይችላሉ። የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ገለል በማድረግና «ይህ ከባህላችን አንዱ ነው። ይህ አኗኗራችን ነው።» በማለት ማመካኛ ምክንያት ሊፈጥሩ ይችላሉ።

እግዚአብሔር በእያንዳንዳቸው በልጆቹ እጅ ኃያሉን መዋጊያ መሣሪያ ጸሎትን አስቀምጧል። የእርሱ ሕዝብ የሚጸልይ ሕዝብ በመሆን መታወቅ አለበት። ይህ መታወቂያው ደግሞ በቅድስና ሕይወቱ መረጋገጥ ይገባዋል። እነዚህ ሁለት ባሕርያት ማለትም የጸሎትና የቅድስና ሕይወት ወንጌልን ለማስፋፋት እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸው ብርቱ ጥምረቶች ናቸው።

አማኞች ከክፉ ኃይላት ጋር በሚደረገው ተግዳሮት ውስጥ እግዚአብሔር ኃይሉን በሚገልጽበት ጊዜ መሣሪያ ለመሆን ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ምሳሌ ለመጥቀስ ቢያስፈልግ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጋንንትን ማስወጣትና በአንዳንድ በሽታዎች ላይ መጸለይን ማመልከት ይቻላል። አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ሆኖ የኢየሱስን ስም በመጥራት ብቻ ኃይልን እንደሚቀዳጅ በቅዱስ ቃሉ ውስጥ የሚገኙ ምሳሌዎች ያመለክታሉ። ደቀ መዛሙርት ስለ ሸባው ለማኝ

መፈወስ በተጠየቁ ጊዜ የሰጡት ምላሽ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነበር። «በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ እንዲህ አላቸው፡- ... በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህ ደኅና ሆኖ በፊታችሁ እንደ ቆመ ...» (ሐዋ. 4፥8-10)። በምዋርተኝነት መንፈስ በተያዘች አንዲት ገረድ ምክንያት ጳውሎስ በተቸገረ ጊዜ መንፈሱን «ከእርስዋ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝሃለሁ አለው» (ሐዋ. 16፥18)። በእንደዚህ ያለ ወቅት የሚገለጠው ኃይል የመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ሁልጊዜ አስታውስ። አማኙ ማገልገል የሚችለው፥ የመንፈስ ቅዱስ መጠቀሚያ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ነው።

ታምራት በራሳቸው ግብ ሳይሆኑ ነገር ግን እግዚአብሔር ኃይሉን ለማሳየትና ሰዎች ወደ ቃሉ እንዲያተኩሩ ለማድረግ የሚጠቀምባቸው ናቸው። «ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ፥ የተናገረውን በአንድ ልብ አደመጡ» (ሐዋ. 8፥6)።

## የሰይጣንን ሥራ ድል ማድረግ

«ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ» (1ኛ ዮሐ. 3፥8)። ሙስሊሞችም ቢሆኑ የእግዚአብሔር ኃይል ተገልጦ የሰይጣንን ሥራ ድል ሲመታ በማየት ይነካሉ። ከዚህ ዓይነቱም አጋጣሚዎች የተነሣ ብዙዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብና ጌታን ለመሻት ተገፋፍተዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ባልደረባ የሆኑት መጋቢ ዴቪድ እስትራቨርስ በምዕራብ አፍሪካ ጉብኝታቸው ወቅት የሰሙትና ያጫወቱኝ ታሪክ ለዚህ ምሳሌ ይሆናል። የባለ ታሪኮቹን ማንነት ለመደበቅ ሲባል ስሞቻቸው ተለውጠዋል።

> ነዋሪዎችዋ መቶ በመቶ ሙስሊሞች በሆኑበት በኤም ከተማ ውስጥ፥ ወንጌላዊው ሙሴ በተለይ የጸሎት ሰው በመሆን ይታወቅ ነበር። ሕዝቡ የሙሴን ትምህርት ባይስማሙም፥ ዳሩ ግን ከመካከላቸው ብዙዎቹ ለየት ያሉ ችግሮቻቸውን ይዘው እንዲጸልይላቸው ወደ እርሱ ይመጡ ነበር።
>
> አንድ ቀን አንዲት ሴት ሣራ የምትባለውን የልጇን ሚስት እንዲጸለይላት ወደ ሙሴ ዘንድ ይዛት መጣች። መንትያ የነበሩት የሣራ ሁለት የመጨረሻ ወንድ ልጆች ታመው ነበር። «የጁ-ጁ ዓይነት ጥንቆላ» ይለማመድ የነበረው ጠንቋይ ሊረዳቸው አልቻለም ነበር። ሙሴ ግን ለልጆቹ ጸለየላቸውና ተሻላቸው። የሣራ ልብ በዚህ ነገር ስለተነካ ከሙሴ ጋር መጽሐፍ ቅዱስ ለማጥናት ተስማማች።
>
> አዲስ አማኞችን ባቀፈው በዚያ በትንሽ ቡድን ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የጥናት ርዕስ ሆኖ የቀረበው በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ የሚገኘው የዮሴፍ ታሪክ ነበረ። ሣራ «እኔም ልክ እንደ ዮሴፍ ሆኜ ይሰማኛል። ምክንያቱም

ቤተዘመዶቹ እኔን ለመጉዳት ይጥራሉ። የጥንቆላ ተግባራቸው ልጆቼ እንዲታመሙ ምክንያት ሆኗል። በዚህም ሊያጠቁኝ ይሞክራሉ እግዚአብሔር ለዮሴፍ ያደረገውን ጥበቃ ሳነብ፥ ለእኔም እንደሚጠነቀቅልኝ እምነት አሳድሮብኛል» አለች። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱ ቀስ በቀስ ወደ ክርስቶስ ታሪክ ጥናት አመራ። ማራም ራሷን የሰጠች ወጣት ደቀ መዝሙር ሆነች። ሆኖም ባለቤቷ አጥባቂ ሙስሊም በመሆኑ በቤተ ክርስቲያን መሰብሰብና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን ለመሳተፍ ይከብዳት ነበር።

ከመለወጧ በኋላ ማራ ስትመሰክር «ስለ ኢየሱስ ከማወቄ በፊት ሁልጊዜ በታላቅ ፍርሃት ውስጥ እኖር ነበር። ብዙ ጊዜ ማታ መተኛት አልችልም ነበር! ልጆቼም ዘወትር ይታመሙ ነበር። ዘመዶቼ ሊያጠቁኝ እንዲያውም ሊገድሉኝ እንደሚፈልጉ አውቃለሁ። በእኔ ላይ የነበራቸው ኃይል ያስፈራኝ ነበር። አሁን ግን አንዳችም ነገር አልፈራም። ምክንያቱም ኢየሱስ ይጠብቀኛል።»

## በጸሎት የሚካሄድ የኃይል ተግዳሮት

ለሙስሊሞች ወንጌልን ለማድረስ በሚገጥመን መንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ ዋናው የመዋጊያ መሣሪያችን ጸሎት ነው። እግዚአብሔር የሰይጣንን ምሽግ በጸሎት አማካይነት እንዴት እንዳፈራረሰ የሚያሳየንን የሚከተለውን ታሪክ የጻፈችው ባለቤቴ ናት።

በሶማሊያ በነበርኩኝ ጊዜ የእስልምና ኃይል በሕዝቡ ላይ ስለሚያሳድረው ጫና በሚገባ እናውቅ ነበር። ስለዚህ ይህንኑ የሶማሌዎችን የእስልምና እምነት ልምምድ ለማጠናከር ወደ ሰፈራችን አንድ ግብፃዊ የሃይማኖት መሪ በመጣ ጊዜ አልደነቀንም። በመስጊድ በሚሰብከበት ጊዜ ሁሉ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ያዳምጠው ነበር። የሚያስደንቀው መልእክቱ ስለ አላህ (እግዚአብሔር) ሳይሆን «ጋላ» (ከሃዲዎች) እያለ በሚጠራቸው ጐረቤቶቻቸው ላይ የሚወርድ የስድብ ውርጅብኝ ነበር። እርሱም በነጋ በጠባ፥ «ልጆቻችሁን ወደእነዚያ ከሃዲዎች ትምህርት ቤት አትስደዱ። እነርሱ ስለ አላህና ስለ ቅዱስ ቁርዓን የሚያስተምሩት ሐሰት ነው። ፈጽሞ ወደ ሆስፒታላቸውም አትሂዱ! የመርዝ መርፌ ይወጉአችኋል» እያለ ያስፈራራቸው ነበር። ከሃዲዎች በማለት የሚያጥላላን እኛን ፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያንን ነው።

ግብፃዊው የሃይማኖት መሪ የሚነዛውን ሐሰተኛ ወሬ ለመቋቋም ምን ማድረግ እንደሚገባን ተቸገርን። በብዙ ሺህ ሙስሊሞች መካከል ያለነው ሚሲዮናዊያን ስምንት ብቻ ነበርን። ደግሞም በሕጋቸው ሥር የምንተዳደር ለአገራቸው እንግዶች የሆንን ሰዎች ነን። ስለዚህ ብቸኛው መሣሪያችን

ጸሎት ብቻ ነበር። በመሆኑም ስለ ትክክለኛነታችን ለማረጋገጥ ጥረት ሳናደርግ ለሕዝቡ አገልግሎት መስጠቱን ቀጠልን። ይህንን በምናደርግበት ጊዜ ሁሉ ኃያሉ እግዚአብሔር ለስሙ ክብር ሲል አብሮን እንዲቆምና አሸናፊነቱን እንዲያስመሰክር በመጸለይ ነበር። ልክ እንደ ኢዮሳፍጥ ነበር የጸለይነው፥ «አምላካችን ሆይ፥ አንተ አትፈርድባቸውምን? ይህን የመጣብንን ታላቅ ወገን እንቃወም ዘንድ አንችልም፤ የምናደርገውንም አናውቅም፤ ነገር ግን ዓይኖቻችን ወደ አንተ ናቸው» (2ኛ ዜና 20፡12)።

ከግብፃዊው የሃይማኖት መሪ የሳምንታት ስብከት በኋላ የገዛ ልጁ እንደታመመበት አወቅን። ስለ እኛ በሕዝቡ ዘንድ ስለተናገራቸው ውሸቶች በሙሉ ኃፍረት ስለተሰማው፥ ለሕክምና ወደ እኛ ዘንድ መምጣት እንደፈራ ሰማን። ሆኖም የልጁ ሁኔታ ተባብሶ ማንቀጥቀጥ ሲጀምረው በጭንቀት ለማበድ የሞከራት እናቱ ትንሹን ልጇን በጨርቅ ሸፍናና እየተቻኮለች ወደ ሆስፒታላችን መጣች።

ለልጁ ሕይወት ያሠጋ የነበረው «የአንጎል ወባ» ብዙ ጊዜ ለሞት የሚያደርስ በሽታ መሆኑን ስለምናውቅ፥ ወዲያውኑ ፈጣን ሕክምና ልናደርግለት ጀመርን። ልጁ በእኛ «በከሃዲዎቹ» ሆስፒታል ቢሞት የሚያስከትለውን መዘዝ ደፍረን ለማሰላሰል እንኳ አልቻልንም። ነገር ግን መርፌ በመስጠትና ትኩሳቱን ለመቆጣጠር ሰውነቱን በየጊዜው በማቀዝቀዝ ርዳታ ማድረጉን ገፋንበት። በሕክምናው አባላት የሃያ አራት ሰዓታት የመጠባበቅ ሥራ ተጀመረ። በዚህ ውስጥ «እግዚአብሔር ሆይ፥ ፈቃድህ ከሆነ ይህንን ትንሽ ብላቴና አስነሣው። ይሁን እንጂ በሕይወት ቢሆን በሞት በሁሉም ስምህን አስከብር» እያልን በመጸለይ ነበር ሥራችንን የምንሠራው።

ሕክምና በተደረገለት በሁለተኛው ቀን ትኩሳቱ ቀነሰ፥ ማንቀጥቀጡም አቆመና ልጁ እየተሻለው ይሄድ ጀመር። በሦስተኛው ቀን ደግሞ፥ ልጁ በደስታ ተሞልቶ በሆስፒታሉ ክፍል ውስጥ ሲጫወት በማየት ከእናቱ ጋር ሆነን በደስታ ፈነደቅን። በዚያን ሌሊት ጨለማን ተገን አድርጐ ከመሬት የሚደርስ ካባ የደረበ አንድ ሰው ወደ ሆስፒታሉ እየቀረበ መጣ። ያ ግብፃዊ የሃይማኖት መሪ እከተማ ሆና የተወዳጅ ልጁን ታምራታዊ ፈውስ ስለሰማ «አመሰግናችኋለሁ» ለማለት ነበር አመጣጡ። ቀደም ሲል ስለተናገራቸው ክፉ ንግግሮች ምንም ይቅርታ አልጠየቀንም። እንደ «ከሃዲ» ከመቆጠራችንም በዚያ ላይ ደግሞ ሴቶች በመሆናችን ይቅርታ መጠየቁ ለእርሱ ውርደት ነበር። ዳሩ ግን ከዚህ ሁኔታ በኋላ ዕንቅፋቱ ቀስ በቀስ ተወገደና ይህ ግብፃዊ ቤተሰቡን ሁሉ ወደ ክሊኒካችን ዘወትር ማምጣት

ጀመረ። እንዲያውም ራሱን ዝቅ በማድረግ ስለ ግል በሽታው ጉዳይ ከቤቷ ዶክተር እንኳ የሕክምና ምክር እስከመጠየቅ ደርሶ ነበር።

ይሁን እንጂ በገጠር የሚኖረውን አንድ ክርስቲያን የሆነ ሱማሌያዊ የክሊኒክ ሠራተኞችንን ለምን «ከሃዲ» ሆንክ በማለት ይኸው የሃይማኖት መሪ ይጨቀጭቀው ነበር። ወጣቱ ክርስቲያን ግን፥ በሕይወቱ ሊደርስበት የሚችለውን አደጋና የስደት መዘዘ ቢገነዘብም፥ የሕይወት ምስክርነቱን ለዚህ ታዋቂ ሰው ከማካፈል ወደኋላ አላለም። ይህ ግብፃዊ የሃይማኖት መሪ ንግግሩን ባደመጠ መጠን ጉጉቱ የቀድሞ ጥላቻውን እያሸነፈው ሄዶ ከልብ የመነጩ ብዙ ጥያቄዎች ያቀርብለት ጀመር። ከዚህም የተነሣ ክርስቲያኑ የዓረብኛ መጽሐፍ ቅዱስን ይዞ ወደ ሃይማኖት መሪው ቤት አዘውትሮ በመሄድ አብረው ያነቡና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርትና ስለ አባባሎቹ ይወያዩ ነበር።

በሶማሊያ ካበረከተው የሁለት ዓመታት ሃይማኖታዊ አገልግሎት በኋላ ያ የእስልምና መሪ አንድ የዓረብኛ መጽሐፍ ቅዱስና እንደዚሁም የክርስቲያኑን ሱማሌና የሚሲዮናውያኑን ጸሎት ይዞ ወደ ግብፅ ተመለሰ። ምንም እንኳ እነዚህ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ለግብፃዊው መሪና ለቤተሰቡ የሰጡት ምስክርነት ሙሉ ፍሬ ሊታወቅ የሚችለው በፍርድ ቀን ቢሆንም፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር በእርግጥ ለስሙ መቆሙን አሳይቷል።

ይህ ታሪክ ቻርልስ ክራፍት የኃይል ተግዳሮት እና የእውነት ተግዳሮት ብለው ስለሚገልጹት ሁኔታ በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው።* እስከ ሞት የታመመው ልጅ ታምራታዊ ፈውስና መነሣት የኃይል ተግዳሮት ነው። ሆኖም ሁኔታው ሙስሊም ቄስ ለሆነው ለአባቱ መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ዕድል አስገኘለት፤ ይህም ከእውነት ጋር ግብግብ በመግጠም ሐቁን ለመረዳት መንገድ ጠረገለት።

* ቻርልስ ክራፍት፥ «በክርስትና ምስክርነታችን ምን ዓይነት ተግዳሮቶች ያስፈልጉናል?» ወንጌላውያን ሚሲዮኖች - በየሦስት ወሩ የሚታተም፥ ሐምሌ 1991፥ ገጽ 258-265 Charles Kraft, 'What kind of encounters do we need in our Christian witness?' EVANGELICAL MISSIONS QUARTERLY, July 1991, p.258-265.

## በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ያለን ድርሻ

** የምንዋጋው በክርስቶስ ካለን የክብር ስፍራ ሆነን እንጂ በምድራዊው ኑሮአችን ተወስነን አይደለም። «በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።» «ከእርሱ ጋር አስነሣን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን» (ኤፌ. 1፡3፤ 2፡6)።

** በክርስቶስ ያለንን ሥልጣን መለማመድ አለብን። «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱ ... እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴ. 28፡18)። «የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል» (ማቴ. 16፡19)።

** እግዚአብሔር በቃሉ የሰጠውን ተስፋዎች የራስህ አድርገህ ቁጠር። «... ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፤ የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም» (ኢሳ. 55፡10፥ 11)።

** ምሽጎችን ለማፍረስ የጦር መሣሪያዎቻችንን በጸሎት ኃይል እንጠቀምባቸው። «የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው» (2ኛ ቆሮ. 10፡4)።

** የክርስቶስ ደም በሰይጣን ላይ ያለውን ኃይል የራስህ አድርገህ ቁጠር። «እነርሱም ሰይጣንን ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት» (ራእይ 12፡11)።

** ሰይጣንን ተቃወም፥ ወደ እግዚአብሔርም ቅረብ። «እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል» (ያዕ. 4፡7-8)።

ለመንፈሳዊ ውጊያ ጠቃሚ የሚሆን «በሥልጣን መጸለይ» የሚል በቲአዶር ኤፕ የተጻፈ መጽሐፍ አለ። የሚከተለው አሳብ ከዚህ መጽሐፍ የተወሰደ ነው።

> «የሰይጣን ኃይል የተሰበረ መሆኑ እውነት ነው (ዕብ. 2፡14፥ 15፤ ቈላ. 2፡15)፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠንን ሥልጣን እስካልተጠቀምንበት ድረስ፥ ሰይጣን እንዴት የያዘውን በዋዛ እንደማይለቅ መገንዘብ ይገባናል። ጸሎት ማለት እግዚአብሔርን ለእርሱ አገልግሎት እናበረክትለት ዘንድ እንዲተባበረን የምናግባባበት መንገድ አይደለም።

ይልቁኑ እኛ ከእርሱ ጋር የምንተባበርበት ጉዳይ ነው። በክርስቲያኑ በኩል የሚደርሰው የእውነተኛ ጸሎት ዓላማ፥ ንብረትነቱ የእግዚአብሔር መሆን ሲገባው በሰይጣን እጅ የወደቀውን ንብረት በእምነት ለመጨበጥና ሰይጣን እስከ ዘለቄታው እስኪባረር ድረስ አጥብቆ መያዝ ማለት ነው። በክርስቶስ ባለን ሥልጣን ላይ ተመርኩዘን ከፉው መንፈስ ከእነዚህ ነፍሳት እንዲርቅ ካልጠየቅን በስተቀር ለምን ጊዜም በቁጥጥሩ ሥር ያቆያቸዋል።»*

* በሥልጣን መጸለይ፥ በቲኦዶር ኤፕ፥ (ሊከን፥ ኤንኢቢ . ወ ደ መጽሐፍ ቅዱስ መመለስ፥ 1965) ገጽ 93። * (Praying with Authority, by Theodore Epp, (Lincoln, ) Neb.: Back to Bible, 1965) P.93.

## በጥልቀት የሚታሰብ

*** ስላለንበት የመንፈሳዊ ውጊያ ይህ መጽሐፍ እንድትረዳ ጠቅሞሃል? ከሆነስ እንዴት?

*** ሰይጣንን ለመዋጋት የጦር ዕቃዎቻችን ምንድን ናቸው?

አንተስ በየትኞቹ ትጠቀም ነበር? በየትኞቹስ ከመጠቀም ነው ቸል ያልከው?

*** ለሕይወትህና ለአገልግሎትህ ጸልየህ ባገኘኸው መልስ ውስጥ የእግዚአብሔርን ኃይል ተለማምደሃል? ምሳሌዎችን ጠቅሰህ ጻፍ።

*** «በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ያለን ድርሻ» ከተሰኘው ሥር የተዘረዘረውን በመከለስ ዘወትር የግልህ አድርገህ ተጠቀምበት።

# ምዕ. 14 አዲስ አማኞችን ደቀ መዛሙርት ማድረግ

አንድ ሙስሊም እንዴ ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመጣ በኋላ ብዙ የፍቅር ድጋፍና ማበረታቻ ይፈልጋል። በጣም ግልጽና ማኅበረሰባዊ የሆነን ሃይማኖት ለቅቆ፥ በማይታይና በልባዊ እምነት ላይ ወደ ተመሠረተ ሃይማኖት መሸጋገር በሙስሊሙ ሕይወት ውስጥ የቱን ያህል ከባድ ለውጥ እንደሚያስከትል መረዳቱ ለክርስቲያኖች ይከብዳቸዋል። አዲሱ አማኝ በሕይወቱ ያለውን ባዶነት የሚሞላ ኅብረት እና ማኅበረሰባዊ ተሳትፎዎች ያስፈልጉታል። ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱን አዲስ አማኝ ያጣውን ቤተሰባዊ ኅብረት በተለወጠ ክርስቲያናዊ ቤተሰብ እንዲተካ ማድረግ ይቻላል። ይህ እንደ እኛ ክርስቲያኖች ሁሉ የእግዚአብሔር ቤተሰብ መሆኑን እንዲለማመድ ይረዳዋል። «በበጐ ፈቃዱ እንደ ወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን» (ኤፌ. 1፡5)።

አዲስ አማኝ የክርስትና እምነቱን እንዲተው ከቤተሰቡና ከጓደኞቹ ሁሉ ከፍተኛ ግፊት ይደረግበታል። ከቤተሰቡም እምነት በማፈንገጡ በእርሱ ላይ የሚሰነዘረው ተቃውሞ ያላቋረጠ ይሆናል። ከሚቀርቡለት ክርክሮች መካከል ጥቂቶቹ ብቸኛና እውነተኛው ሃይማኖት እስልምና እንደሆነ፥ እስልምናን የሚተው ይቅር የማይባል ኃጢአት እንደፈጸመ፥ ብሎም በቤተሰቡና በማኅበረሰቡ ላይ ከፍተኛ ውርደት እንዳስከተለና የመሳሰሉት ናቸው። ለዚህ አድራጎቱም በአጸፋው የሚወሰዱበት ተጨባጭ እርምጃዎች፥ ከቤተሰብ መገለል፥ ከቤት መባረርና እስከ ግድያም የደረሰ ሊሆን ይችላል።

ስለዚህ አንተ የእግዚአብሔርን ቃል መመሪያውና ኃይሉ ማድረግን እንዲለማመድና በተቃውሞም መካከል መቆም እንዲችል፥ እንደዚሁም በእግዚአብሔር ቃል ሥር እንዲሰድ ለማድረግ ጊዜ በመውሰድ በትዕግሥት አስተምረው። በመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጡትን ተስፋዎች ወስዶ የእርሱ አድርጎ በመቁጠር መልሶ ለእግዚአብሔር እንዲጸልይ አስተምረው። ተገቢውን ጥንቃቄ የተሞላ አቀባበልና ክብካቤ ከሚሰጠው የክርስቲያኖች ኅብረት ጋር ማገናኘት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ በተለይ በመጀመሪያዎቹ የሽግግር ጊዜያት አንገብጋቢነት አለው። ከክርስቲያኖች ጋር ስለፈጠረው አዲስ ጥብቅ ኅብረት ቤተሰቡ ጣልቃ እንዳይገባ በተቻለ መጠን ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

ይሁን እንጂ ከሚገባ በላይ በሰዎች ላይ እንዳይደገፍ ማሞላቀቅ መወገድ አለበት። አለበለዚያ ለችግሮቹ ሁሉ ራሱን በእግዚአብሔር ላይ መጣልን ሳይማር ይቀራል።

እምነቱን በተመለከተ አንድ አዲስ አማኝ፥ ለቤተሰቡና ለማኅበረሰቡ ክርስቲያን መሆኑን ከመግለጹ በፊት ምን ምክር ሊሰጠው ይገባል? እያንዳንዱ ሁኔታ የተለየ ስለሚሆን ለሁሉም የጋራ የሚሆን መልስ የለም። ስለዚህ ሁኔታ የሚገልጽ አንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማጣቀሻ በሮሜ 10፡9 ላይ ይገኛል፥ «ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና»። ስለዚህ አመቺ በሆነ ቦታና መንገድ የኢየሱስን ጌትነት መግለጽ ያስፈልጋል።

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በዓመታት መካከል ሁለት የአስተሳሰብ ክፍሎች ብቅ ብለዋል። የመጀመሪያው አሳብ አዲስ አማኝ በድፍረት ጌታን ለመከተል ለቤተሰቡ እና ለአካባቢው ኅብረተሰብ ለመመስከር በዚህም ረገድ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ለመፈጸም ያደረገውን ውሳኔ ለቤተሰቡና ለአካባቢው ኅብረተሰብ ለመመስከር ይገባል የሚል ነው። ይህ ብዙ ጊዜ የሚያስከትለው ውጤት ከሁለት አንድ ነው፤ ወይ ይገደላል፥ አለበለዚያም ሕይወቱን ለማትረፍ ሲል ከአገሩ በመሸሽ በአንዳንድ ክርስቲያን ቡድኖች ሥር ጥገኝነት ይጠይቃል።

ሁለተኛው አሳብ የተለወጠው ሰው ስለ ውሳኔው ምንም ሳይናገር በማኅበረሰቡ ውስጥ እንደ ቀድሞው መቀጠልና እምነቱን ለመመስከር ጌታ ዕድሉን በትክክለኛው ጊዜ እስኪሰጠው ድረስ በመተማመን መቆየት ያስፈልገዋል የሚል ነው። እያንዳንዱ ዕቅድ የራሱ ጥቅሞችና ጉዳቶች ቢኖሩትም፥ ሆኖም ግን የትኛውም ዕቅድ ቢሆን ለተለወጠው ሰው በሕይወት መቆየት እና መንፈሳዊ እድገት ዋስትና አይሰጥም።

በበኩሌ ከሁለቱ የውሳኔ እርምጃዎች ይኸኛው ይሻላል ብዬ ለመናገር ብቃት አይሰማኝም፤ ነገር ግን ክርስቲያኖች አዲስ አማኝን ለመምራት ከእግዚአብሔር ጥበብን እንዲጠይቁ እመክራለሁ። የጌታን ሰዎች ሰማዕት እንዲሆኑ ለመገፋፋት የተጠራን አለመሆናችንን መረዳቱ ተገቢ ይመስለኛል። አንዳንዶቹ በአደባባይ መናገሩን ቢመርጡም፥ እኛ ግን አዲስ አማኞች ይህን እንዲያደርጉ መገፋፋት የለብንም። ምንም እንኳ አንዳንዶቹ ስለ አዲሱ እምነታቸው ከሁኔታዎች የተነሣ ለመመስከር ባይችሉም፥ በሕይወታቸው ያለውን የጌታ በረከት ይገነዘባሉ። አንዳንድ የተለወጡ ሰዎች በቤተሰባቸው ጥብቅ ቁጥጥር ውስጥ ከመሆናቸው የተነሣ ክርስቲያናዊ ኅብረት የሌላቸውና እንደ ሙስሊም የሚቀበሩ ናቸው። ማንም ሰው የትም ቢቀበር እውነተኛ አማኝ ከሆነ ከመቃብር ይነሣል፥ ጌታ ሕያዋን እንደሆኑ ያውቃል።

ኤልያስ በእስራኤል የቀረው እርሱ ብቻ እንደሆነ በማሰብ ለጌታ ምሬቱን በገለጸ ጊዜ፥ ለበኣል ያልሰገዱ ሌሎችም 7000 ሰዎች መኖራቸው ሲነገረው ደነገጠ። ይህ ዛሬ የምሥጢር አማኞች ለሆኑት ተመሳሳይነት አለው (1ኛ ነገ. 19፡18)።

ልክ የምስክርነትን ጥያቄ አንግበው የሚነሡ የተለያዩ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ፥ የጥምቀትንም ጥያቄ የሚያነሡ አሉ። በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዘንድ ለጥምቀት ሥርዓት የሚሰጠው ክብደት የመጨረሻው ከፍተኛ ነው። ይህም ከአእምሮአቸው ውስጥ እጅግ በመስረፁ ነገሩ ቀላል ተደርጐ መወሰድ የለበትም። ይህም እንደገና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ክርስቲያኖች ውሳኔ ሆኖ ይሰማኛል። የግል ስሜቴ ግን፥ አዲሱ አማኝ ይህን ቁራጥ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ቃሉን በትክክል የተረዳና ለመንፈሳዊ እድገቱም አሳማኝ ማረጋገጫ ያሳየ መሆን ይገባዋል የሚል ነው።

አንድ ሙስሊም በሚለወጥበት ጊዜ ታሪኩን አደባባይ ማውጣት ወይም ግለሰቡን በግላጭ ማቅረብ አለማስተዋል ነው። እጅግ ጥሩ መመሪያ የሚሆነው ለሙስሊም ማኅበረሰብ ወይም ለሰይጣን የተለየ ዒላማ የሚያደርገውን ማንኛውንም ነገር አለማድረግ ነው። በምሥጢር ሊያበረታቱትና ሊጸልዩለት ለሚችሉ ክርስቲያኖች መንገር ነው አስተማማኝነት ያለው። ምስክርነቱን ለቤተሰቡና

ለጓደኞቼ ለመንገር በተዘጋጀ ጊዜ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲመራው መተው ነው።

በመስጊድና በወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የሚካሄዱ የአምልኮ መልኮች የተለያዩ ናቸው። ወደ መስጊድ ከመግባቱ አስቀድሞ አምላኪው ሃይማኖታዊ መንጻትንና ጫማ የማውለቅ ሥርዓትን ማከናወን አለበት። የእምነት መግለጫና ጸሎቶች በአነስተኛ ድምጽ በቃል የሚነገሩት እንደቆሙ ነው። በተወሰነ ጊዜ ሁሉም ሰው ይንበረከክና ከዚያም በግምባሩ ይደፋል። ኢማሙን (ሰባኪውን) በሚያዳምጡበት ጊዜ ሁሉም አምላኪዎች በወለል ላይ ይቀመጣሉ።

ስለዚህ ሙስሊም ጓደኛህን ወደ አምልኮ አገልግሎት ለመጋበዝ ከሚገባ በላይ አትጓጓ። የጋራ መተማመኛችሁ እየጸና ሲሄድ ምናልባት ጓደኛህ ከአንተ ጋር አምልኮውን ለመሳተፍ ይጠይቅ ይሆናል። ከዚያ በአምልኮው ውስጥ ሊገጥመው የሚችለውን ለመግለጽ ጊዜ መውሰድና በአገልግሎቱም ወቅት በጥንቃቄ መምራት ያስፈልግሃል። ስለ መምጣቱም ከጉባኤው አንዳንዶቹ እንዲያውቁት አድርግ። የወዳጅነት መንፈስ እንዲያሳዩትና እንደ ሰው እንዲቀበሉት አበረታታቸው።

በጣም ቀናኢ ምስክርነትን ከሚሹ ጠያቂዎች ተከላከልላቸው። አንድ ጊዜ ሊደርስ የሚችለውን ነገር አስቀድሜ ባለመጠራጠር፥ አንድ ቱርካዊ ባልና ሚስት ይዤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄድኩኝ። ከአስተዋወቅኋቸው ሰዎች አብዛኛዎቹ ለእነዚህ ባልና ሚስት ትሕትናና የወዳጅነት መንፈስ ያሳዩ ነበሩ። ሆኖም ግን አንድ ቅንነት ያልጐደለው አባል ምንም ስለማያውቀው እስልምና በመቀባዠር ባልና ሚስቱን አስጨነቃቸው። በሁኔታው ስለተንገሸገሽኩኝ ጣልቃ ገባሁኝና እነዚህ ቱርካውያን ጓደኞቼን ከሰውዬው አላቀቅሁዋቸው። ከዚያን ጊዜ በኋላ ለእነዚያ ወዳጆቼ ለክርስትና ጨርሰው ጀርባቸውን እንዳይሰጡ ልዩ እንክብካቤ ላደርግላቸው አስፈልጎ ነበር።

ብዙውን ጊዜ ቀድሞ ሙስሊም የነበሩትን መቀበልና በክርስቶስ ወንድሞች አድርጎ ማመን ለክርስቲያኖች ይከብዳል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ከሙስሊሞች ጋር ቀደም ብሎ ከነበራቸው የጥላቻ አመለካከት የተነሣ ነው። በከፍተኛ የሥነ መለኮት ትምህርት በዩ ኤስ ኤ የዶክትሬት ዲግሪ የተሰጠውን አንድ ሰው አውቃለሁ። ነገር ግን በሚያስተምርበት በገዛ አገሩ የነበረው የክርስቲያኖች ዝንባሌ «ምንስ ዓይነት ነገር ቢሆን እንዴት ሊያስተምረን ይችላል? እርሱ ሙስሊም የነበረ ነው» የሚል ነበር።

ክርስቲያኖች ማስታወስ ያለባቸው በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የነበረው ግድግዳ በአዲስ ኪዳን ዘመን በክርስቶስ መፍረሱን ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ አሁንም ክርስቶስን በሚከተሉ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች መካከል ያለው ግድግዳ ፈርሷል። አዲስ አማኞችን «የቀድሞ ሙስሊሞች» ብሎ አዘውትሮ መጥቀሱ

ክብርን ማሳጣት ነው። እንዲሁም ከአረማዊነት የተመለሱ ክርስቲያኖች ሁልጊዜ «ቀድሞ አረማዊ ነበሩ» እየተባለ እንዲነገርባቸው አይፈልጉም።

የክርስቲያን የአምልኮ አገልግሎት አካሄድ ለአዲስ አማኞች ከባድ ሊሆን ይችላል። ሆኖም፣ የማይፈታ ችግር አይደለም። ግን እንገብጋቢ ጉዳይ ሆኖ ከተገኘ በእርግጥ ጥንቃቄ ያልተለየው አያያዝ ይጠይቃል። አንዳንድ በሙስሊሞች መካከል የሠሩ ሰዎች ይህን ችግር ለመወጣት ከሙስሊምነት የተለወጡትን የሚያቅፍ ቤተ ክርስቲያን መመሥረት ያስፈልጋል ብለው ይናገራሉ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሙስሊምነት ለተለወጡት አምልኮን ጣዕም ያለው ለማድረግ መርሆዎችን በማጥናትና በመገምገም ሊታገዙ ይችላሉ።*

* አዲስ ጐዳና በሙስሊም ወንጌል ስርጭት፣ በፊል ፓርሻል፣ ምዕራፍ 7፣ ግራንድ ራፒዲስ፣ ኤም አይ፡ ቤከር ማተሚያ ቤት፣ 1980። * New Paths in Muslim Evangelism, by Phil Parshall, Chapter 7, Grand Rapids, MI: Baker Book House, 1980.

(ማስታወሻ፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ነገሩን ለማሳጠር እንዲረዳ በአጠቃላይ በወንዴ ጾታ ተጠቅመናል።)

## በጥልቀት የሚታሰብ

*** ልባዊ የሆነ ሙስሊም ወደ ቤተ ክርስቲያን እንድትጋብዘው ቢጠይቅህ ታቅማማለህ? ከሆነ ለምን?

*** ለቤተ ክርስቲያንህ ምእመናን ከእንግዳ ሙስሊም ጋር ስለመተዋወቅ ምን መመሪያ ትሰጣለህ?

*** አንድ አዲስ የተለወጠ ሰው በክርስቶስ ያለውን እምነት በገሃድ መናገር አለበት? ከሆነ መቼና በምን ዓይነት ሁኔታ?

# ክፍል 3

# ሙስሊሞችን የመድረስ ስልት

## ምዕ. 15 የእርስ በርስ መቀራረብ

ባለህበት አካባቢ ለወንጌል ስርጭት ሊጠቅሙ የሚችሉ አንዳንድ አሳቦችን ላቀርብልህ እፈልጋለሁ። ክርስቲያኖች ያሉአቸው የነፃነት ደረጃዎች ከአገር ወደ አገር ስለሚለያዩ ሁሉም አሳብ ተስማሚ ላይሆኑ ይችላል። በግል ሁኔታህ በመንተራስ በእነዚህ አሳቦች መጠቀም፥ ማሻሻል ወይም መተው ትችላለህ።

ፍሬያማ ምስክርነት በእኛ ብልሃት ላይ እንደማይወሰን በማወቅ ተበረታታ። ታማኝነታችን የሕይወት ጽናታችንና እንደዚሁም ግንኙነታችን ለምስክርነታችን ቃል ማስረጃ ሊሆኑ ይገባል። ሕይወታችን የክርስቶስ መዓዛ ሊሆን ይገባል (2ኛ ቆሮ. 2፡16)። የሙስሊሞች ደኅንነት የጌታ ሥራ ሲሆን ዓላማዎቹን ለመፈጸም ይጠቀምብናል። ለጌትነቱ ራሳችንን ስናስገዛ እርሱ ይመራናል።

የጋራ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች በአንድነት መጣመራቸውና አንዳንዴም ለሌሎች መሰናከል መፍጠራቸው የሕይወት እውነታ ነው። እንዲህ ያለውን ድርጊት ሙስሊሞች በሚፈጽሙበት ጊዜ ድንበሩን ለማቋረጥ መሻት ያለባቸው ክርስቲያኖች ናቸው።

### 1. ወዳጅነትና መስተንግዶ

በፍቅር ለሰዎችና ለቤተሰቦች ወንጌል ማድረስ ወዳጅነት ለመፍጠር እጅግ ቀና የሆነ መንገድ ነው። ማንም ሰው እርሱን እንዲወዱት ይፈልጋል። እውነተኛ ፍቅርን የሚጋፉ ልብ ቢኖር በጣም ደንዳና የሆነ ልብ ነው። ሙስሊሞችን ለመድረስ ቁልፉ ይህ ነው። ይህ ደግሞ እንደማገኘውም ሰው ለእነርሱም ከልብ የመነጨ የመጠበብ ስሜት ሊኖር ይገባል። ለእነርሱ ያለህን በጐ ፍላጐት የምትገልጽባቸውን ዕድሎች ፈልግ። ምናልባት የታመመን መጠየቅ፥ ጭምት አስተዛዛኝ በመሆን በቀብር ሥነ -ሥርዓት ላይ መገኘት፥ ወይም በሃይማኖታዊ በዓሎቻቸው ላይ መካፈል ሊሆን ይችላል። ስለ በዓሎቻቸውና ለምን እንደሚያከብሯቸው ጠይቅ። ይሁንና ፍላጐትህ ሐቀኛና ከፈራጅነት መንፈስ የራቀ ሊሆን ይገባል። ሆኖም ይህን የመሳሰለውን ጊዜ፥ ለመስበክ ያጋጠመህ ዕድል አድርገህ ልትጠቀምበት አትሞክር። እስልምና ከክርስቲያኖች ጋር የወዳጅነት ምሥረታን ስለማያበረታታ አነሣሽነቱ መምጣት ያለበት ከጌታ ሰዎች አቅጣጫ ነው።

ይህ የወዳጅነት አቀራረብ ጊዜን፣ ትዕግሥትንና ጽናትን የሚጠይቅ ነው። የወዳጅነት ግንኙነቶች ከተመሠረቱ ወዲያ መስተንግዶ መለዋወጥ ይቻል ይሆናል። በቤትህ ነፃነት እንዲሰማቸው የሚያስቀይሟቸውን ድርጊቶች ከማድረግ በመቆጠብ ጥንቃቄ አድርግ። ቀጥሎ ይህን ጉዳይ በተመለከተ አንዳንድ አሳቦች ቀርበዋል።

* ሙስሊም ወዳጆችን ለግብዣ ከመጥራትህ በፊት የሚስማማቸው ምግብ ምን እንደሆነ ጠይቅ። የአልኮል መጠጥ ወይም የአሳማ ሥጋ አታቅርብ።

* በግድግዳዎች ላይ «የተቀደሱ» ሥዕሎችን፣ መስቀሎችን፣ ወዘተ. አትስቀል። በደንብ (ባማረ ሁኔታ) የተጻፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች /ጥቅሶች/ ግን ተቀባይነት አላቸው።

* ከማዕድ በፊት፣ «ስለዚህ ምግብ ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቅርብ» በላቸው። ይህን ብቻ እንጂ ሌላ ነገር አትናገር። «ጸሎት» የሚለውን ቃል አትጠቀም! ምክንያቱም ቃሉ በተጋባዦችህ ዘንድ ሥርዓታዊ ጸሎት የሚል ትርጓሜ ነው የሚሰጣቸው።

* መጽሐፍ ቅዱስህን በታላቅ ክብር ያዘው። ከሙስሊሞች ጋር ሆነህ የምትጠቀምበት መጽሐፍ ቅዱስ በእጅ የተጻፉ ማስታወሻዎች ያሉት ወይም መስመሮች የተሰመሩበት መሆን የለበትም። ምክንያቱም እንዲህ ያለውን ድርጊት የተቀደሰውን መጽሐፍ እንደማርከስ አድርገው ስለሚወስዱት ነው። በወለል ላይ፣ ከበስተኋላህ ወይም በላዩ ላይ ምንም ነገር አታስቀምጥ። በጨርቅ መለበድ ምን ያህል እንደምታከብረው የሚገልጽ መንገድ ነው።

በጥቅሉ ከቃሉ ጋር የማይጋጭ ከሆነ የሙስሊሞችን ባህላዊ አቀራረቦች ተከተል። ስለ ጌታ ኢየሱስ ለመናገር ትዕግሥት ይኑርህ። መንፈስ ቅዱስ ለመናገር በሩን እስኪከፍትልህ ጠብቅ። ቀደም ሲል በዚህ መጽሐፍ እንደተገለጸው የቃል ማካፈል ትኩረት የሚያነጣጥረው በአንገብጋቢ መንፈሳዊ ፍላጎቶቻቸው ወይም ችግሮቻቸው ላይ መሆን ያስፈልገዋል። ይህን ለማድረግ ጊዜ ውሰድ። ፍጥጫንና ክርክርን አስወግድ። ከእነርሱ የሚመጣውን ምላሽ በመጠቀም ስለ ጌታ ኢየሱስ ተናገር።

## ለልባዊ ዝንባሌ የሚደረግ ቅድመ-ጥንቃቄ

ስለ ጥብቅ ወዳጅነት የጥንቃቄ አስተያየቴን ላካፍላችሁ። እንዲህ ባሉ ውይይት አነሣሽ አቀራረቦች ልባዊ ዝንባሌህን በተመለከተ ማንኛውም ዓይነት አለመረዳት ቢኖርብህ አስወግደው። ወንዶች ለወንዶች ብቻ ሴቶች ደግሞ ለሴቶች ብቻ ነው ወዳጅነት ማሳየት ያለባቸው። ይህም በድንገተኛ ሁኔታ እንኳ ሳይቀር በተቃራኒ ፆታዎች መካከል የቀረበ ግንኙነት እንዳይፈጠር ነው። ለምሳሌ ክርስቲያን የሆነ ወንድ ሙስሊም ቤት ሄዶ ባልዩው አለመኖሩን ካወቀ ወዲያውኑ መመለስ አለበት። ወይም አንድ ሙስሊም ወንድ ባሏ በሌለበት ጊዜ ወደ ቤቷ

ቢመጣ ክርስቲያኒቷ ሴት ማድረግ ያለባት ባሏ በሚኖርበት ጊዜ እንዲመጣ መንገር እንጂ፥ ወደ ቤት መጋበዝ የለባትም። በእርግጥ ሙስሊም ባልና ሚስት ከክርስቲያን ባልና ሚስት ጋር አብረው በመሆን መካፈል ይችላሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ለወንጌል ፍላጐት የሚያሳዩ ሙስሊሞች ልባዊ ዝንባሌ መገምገም አለበት። ቃሉ «እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብ የዋሆች» (ማቴ. 10:16) እንድንሆን ያዝዘናል። ይህ ምክር ደግሞ ከሙስሊሞች ጋር በሚኖረን ጉዳይ ልንከተለው የተገባ ነው። በዚህ ረገድ ክርስቲያን ወጣት ልጃገረዶች ከሙስሊም ጠያቂ ጋር በሚሆኑበት ጊዜ ከማንኛውም ዓይነት ስሜት ቀስቃሽ ሁኔታ መቆጠብ አለባቸው። ሙስሊሞች ክርስቲያን ሚስቶችን ለማግኘት ሲሉ የተለወጡ ለማስመሰል ይችላሉ። አንዳንድ ሙስሊሞች ደግሞ የክርስቲያን ኅብረቶች ውስጥ በሰላይነት ሠርገው ሊገቡ ይፈልጉ ይሆናል። ሌሎች ደግሞ ለግል ጥቅማቸው ሲሉ በተለያዩ መንገዶች በክርስቲያኖች ለመጠቀም ይሞክሩ ይሆናል።

ለሙስሊም ሴቶች የሚደረግ የተለየ አገልግሎት «ፍቅር» በሚለው ምዕራፍ ውስጥ የሙስሊም ሴቶች ልዩ ችግር (ፍላጐት) ተጠቅሷል። ክርስቲያን ሴቶች፥ ሙስሊም እህቶቻችሁን ለመድረስ ልባችሁን ክፈቱ። ለእነርሱ ለመጸለይ ልዩ ሸክም እንዲሰማችሁና የጌታ ኢየሱስ ፍቅር እውነት እንዲሆንላቸው ለማድረግ የጥበብ መንገዶችን እንዲገልጽላችሁ ጌታን ጠይቁ። ስለ አንገብጋቢ ፍላጎቶቻቸው፥ ስለ ፍርሃቶቻቸው እና ጥርጣሬዎቻቸው፥ ስለ ልጆቻቸው የወደፊት ዕድል በማንሣትና በመወያየት፥ ለወዳጅነታችሁና ለፍቅራችሁ መግለጫ መንገድ በማድረግ ተጠቀሙበት። በምትወዳቸው ጊዜ በራስ የመተማመን ስሜታቸው እንዲዳብርና ዓላማቸውን ለማሳካት እንዲችሉ ገንቢ አስተያየቶችን ሰንዝሩላቸው።

ቁርዓን እንዲህ ይላል፡- «ወንዶች በሴቶች ላይ ቋሚዎች (አሳዳሪዎች) ናቸው! አላህ ከፊላቸው በከፊሉ ላይ በማብለጡና (ወንዶች) ከገንዘባቸው (ለሴቶች) በመስጠታቸው ነው። መልካሞቹም ሴቶች (ለባሎቻቸው) ታዛዦች፥ አላህ ባስጠበቀው ነገር ሩቅን ጠባቂዎች (2) ናቸው። ...» (ቁርዓን 4:34)። የሙስሊም ሥነ-መለኮት ጠበብት ይህንን ጥቅስና የመሳሰሉትን እውቂያ እንዲያገኙ የተቻላቸውን ያህል ይገፋፋሉ። ቁርዓንን የሚፈታው ሐዲስ ወይም ወግ፥ ሴቶች እውቀት፥ ሃይማኖትና አመስጋኝነት እንደሚጐድላቸውና ስለዚህም ጠቀሜታቸው ለባርያነት ብቻ እንደሆነ ይናገራል። «የአላህ ሐዋርያ አንድ ጊዜ ለሴቶች እንዲህ ሲል ተናግሯል፥ «ከእናንተ ይብስ እውቀትና ሃይማኖት የጐደለው ማንንም አላየሁም።» ሴቶቹም ጠየቁ፥ «የአላህ ሐዋርያት ሆይ፥ በእውቀታችንና በሃይማኖታችን የሚጐድለው ምንድን ነው?» እርሱም እንዲህ አለ፥ «የሁለት ሴቶች ምስክርነት ከአንድ ወንድ ምስክርነት ጋር እኩል አይደለም ወይ?» በአወንታ መለሱለት። እንደገናም «ሴት በወር አበባዋ ወቅት መጸለይ ወይም መጾም አለመቻሏ እውነት አይደለም ወይ?» አሁንም ሴቶቹ በአዎንታ መለሱለት።

እርሱም «በሃይማኖታችሁ ያለው ጉድለት ይህ ነው» አላቸው * ሳሂህ ቡካሪ፥ ቅጽ 1፥ ሐዲስ ቁ. 301።

ባለቤቱ በሙስሊም ምድር የሕክምና ዶክተር ሆና ለብዙ ዓመታት ሠርታለች። በዚህ አገልግሎቷ ሙስሊም ሴቶች ስለ ራሳቸው እንዴት እንደሚያስቡ ግንዛቤ ማግኘት ችላለች። በኅብረተሰብ ውስጥ ያላቸው ስፍራ በጥቅሉ ከወንድ ጋር ባላቸው ግንኙነትና ተገዢነት ላይ የተመሠረተ ነው። «የዓሊ ልጅ፥ የአብዲ ባለቤት፥ የዩሱፍ እናት»፥ ተብለው የሚጠሩ ነገር ግን በግል መብት ምንም ቦታ የሌላቸው ናቸው። ይህ የከብራቸው መጉደፍ ገና ከልጅነት ስለሚጀምር ለእግዚአብሔር ውድ መሆናቸውንና እርሱም እንደሚወዳቸው እንዳይረዱ ችግር ይፈጥርባቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ ዘንድ ወንድም ይሁን ሴት እኩል ክብር እንዳላቸው በግልጽ ያስተምራል (ገላ. 3፡28)። አለመታደል ሆኑና ለወንድ ልጆች አድሎ የማሳየት ኃጢአታዊ ልምምድ ዓለም አቀፋዊ መልክ የያዘ ይመስላል። ስለዚህም ይህ ሁኔታ ጠንክሮ በማስተማርና በክርስቲያኖች የሕይወት ምሳሌነት መስተባበል አለበት።

ሙስሊም ሴቶች በመካንነት ወይም ወንድ ልጅ ባለመውለድ የተነሣ ከትዳራችን እንፋታለን በማለት በፍርሃት ይኖራሉ። መፋታት ማለት ልጆችዋን ተነጥቃ ከቤተሰቧ (አባት፥ ወንድም፥ አጐት) በጥገኝነት እንድትኖር ትገደዳለች ማለት ነው። እነዚህ ቤተዘመዶችዋ የማይቀበሏት ከሆነ ያላት ብቸኛ መውጫ ሴትኛ አዳሪነት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ በኅብረተሰብ ውስጥ ያላትን ክብር በማጣት በራሷ ላይ የልብ ስብራት፥ ውርደትና ኃፍረት ታመጣለች።

ከሙስሊም ሴት ጋር መቀራረብ የምትጀምሪው በምትወልድበት ጊዜ ለሕፃኑ ትንሽ ስጦታ ይዘሽ ሄደሽ በመጠየቅ ሊሆን ይችላል። እንደዚሁም ከቤተሰቡ ሰው ሲታመም መጠየቅ ትችያለሽ። ተቀባይነትን ካተረፍሽ በኋላ ሁኔታው ጤናማና የወዳጅነት መንፈስ የሰፈነበት ከሆነ ለታመመው ሰው ለመጸለይ ጥያቄ ማቅረብ ትችያለሽ። ክርስቲያን ብቻ ከመባል «የመጽሐፍ ሰው» ተብለሽ የምትታወቂ ቢሆን ጠቃሚ ነው። ይህ ለምትጐበኚያቸው ቃሉን ለማንበብ ዕድል ይከፍታል። የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና፥ መንፈስ ቅዱስ የሙስሊሞችን ልብ ለመንካት የሚጠቀምበት ብርቱ መሣሪያ መሆኑን አስተውዪ።

የአንድ ቤተ ክርስቲያን ቡድን የሙስሊም ሴቶችን ልብስ መቅደድና መስፋት እንዲሁም ጥልፍ ያስተምር ነበር። በርከት ያሉ የስፌት መኪናዎች አግኝተው ነበርና ጧት ጧት አጠቃቀማቸውን ያስተምሯቸው ነበር። ከሰዓት በኋላ መኪናዎቹን ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው ወይም በሽያጭ ልብስ እንዲሰፉባቸው ነፃ ይደረጉላቸው ነበር። ሥራው ሙስሊም ሴቶች የኑሮአቸውን ዘይቤ እንዲያሻሽሉ እና እንደ ማንኛውም ሰው ያላቸውን ክብርና ብቃት ለማረጋገጥ የሚረዳ አገልግሎት ነው።

ይህ ርዳታ የሚደረገው በክርስቲያናዊ አመለካከት ነው። የስፌት መኪናዎቹ በሚገኙበት ክፍል ግድግዳ ላይ በርካታ ማራኪ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተሰቅለዋል። ይህ ሁሉ በሚደረግበት አገር ወንጌልን መናገር በጥብቅ በመንግሥት የተከለከለ ነው። ይሁን እንጂ ሴቶቹ ስለ እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጉጉት እያደረባቸው ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ። በዚህ ጊዜ ክርስቲያኖች ትርጉማቸውን ለማብራራት ዕድል ያገኛሉ። ማስተማሩና መወያየቱ አብረው የሚካሄዱበት ይህ ሁኔታ የጌታ ኢየሱስ እውነት የሙስሊሞችን ልብ እንዲከፈት ምክንያት ሆኗል።

ሌሎች ሙያዎችን፣ ለምሳሌ በአካባቢ ቋንቋ መሠረተ ትምህርትን፣የእንግሊዝኛ ቋንቋ ታይፒንግ/ኮምፒዩተር እና የጸሐፊነት ሙያን የማስተማር ዕድሉ ሊኖር ይችላል። እንዲህ ያሉ ትምህርቶች ለወንጌል ስርጭት ተቀባይነት ያላቸው በሮችን ይከፍታሉ።

ዕድሉ በተገኘ ጊዜ ሁሉ ክርስቲያን ሴቶች በጋብቻቸው ያላቸውን ዋስትና ማሳየቱ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም በባልና ሚስት መካከል ያለውን የእርስ በርስ መከባበርና መዋደድ፣ አንዱ ለሌላው ያለውን ራስን የመስጠት ፈቃደኛነትና በዚህ በባልና ሚስት አንድ ለአንድ በሆነ ግንኙነት ማንም ጣልቃ መግባት ያለመቻሉን መግለጽ ማለት ነው። ይህ ለሙስሊም ሴቶች የተለየ ጠቀሜታ አለው። የእነርሱ ጋብቻ የሚከናወነው በቤተሰብ አማካኝነት ነው። ወንዶቹ ደግሞ በአንድ ጊዜ አራት ሚስቶች ማግባት የተፈቀደላቸው ስለሆነ፣ አንዲት ሴት ባሏን ከሌሎች ሚስቶችና ልጆቻቸው ጋር የመጋራት ዕጣ ላይ ትወድቃለች። የክርስቲያን ጋብቻ የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ግንኙነት አምሳል በመሆኑ፣ በክርስቶስ ያለው ሕይወት ምን እንደሚመስል ሕያው ምስክር ነው።

የእግዚአብሔር ውብ ፍጥረት የሆነችው ሴት፣ እንደ እኩያ ጓደኛ ሆና ወንድን እንድትረዳ የተፈጠረች ናት። በእስልምና ግን በባሏ እጅ እንዳለች አሻንጉሊት ያክል ዝቅተኛ ስፍራ የተሰጣት ናት። ያላት ድርሻ ማንኛውንም ስሜቱን ማርካትና የሌሎችን የቤተሰብ አባላት ፍላጐት ማሟላት ነው። በዘመናዊው የከተማ ሕይወት አንዳንድ ነፃነት ስላለ የትምህርት ዕድል ያገኛሉ። ይሁን እንጂ አክራሪ ሙስሊሞች ሴቶች ወደነበሩበት የጭቆና ስፍራ እንዲመለሱ እየታገሉ ናቸው።

እንደ እኔ ትዝብት ከሆነ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ መንፈሳዊ መነቃቃት አላቸው። እስቲ ወንጌላትን ሁሉ አንብብና በምድራዊ አገልግሎቱ ወቅት በጌታ ኢየሱስ ላይ ያመፁ ሴቶች ስንት እንደሆኑ ቁጠር። ዘገባዎች እንደሚያሳዩት አንዲት ሴት እንኳ አልነበረችም።

በሙስሊም ወንጌል ስርጭት ዋናው ስልታዊ ዕቅድ አባ ወራዎችን መድረስ እንደሆነ አልፎ አልፎ ይነገራል። ይህ አስፈላጊ ቢሆንም ዳሩ ግን የተሟላ መልስ አይደለም። ስልታችን ምንም ይሁን፣ ክርስቲያን ሴቶች ለሙስሊም ሴቶች ወንጌልን ማድረሳቸውን ያካተተ መሆን አለበት።

## የወዳጅነት ማዕከሎች

በከተማ ውስጥ የምትኖር ከሆነ፥ ሙስሊሞችን ለመድረስ መገናኛ ማዕከል መፍጠር ይቻላል። ይህ ጥያቄዎችን ለውይይት ለማቅረብ፥ ጽሑፍ ለማንበብ፥ ካሴት ለማዳመጥ ወይም ቪዲዮና ፊልሞችን ለመመልከት የሚችሉበት ዓይነት ጸጥተኛና ገለልተኛ ስፍራ መሆን ያስፈልገዋል። ይህ ዓይነት የውስጥ ድርጅት አዲስ አሳብ ለመቀበል አእምሮአቸው ክፍት ለሆነ ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ ሳቢነት አለው።

## በባህላዊ ሁኔታዎች ተጠቅሞ ወንጌልን ማካፈል

ከሙስሊሞች ጋር ወዳጅነቱ እንደ ከተመሠረተ በኋላ የክርስቲያን በዓላት፥ ሠርግ እና ክብረ በዓላት ወንጌልን ለማካፈል እጅግ ጥሩ ዕድሎች ናቸው። ተራ ዓለማዊ በዓላት አድርገው ለሚመለከቱአቸው ሙስሊሞች የጌታችን ልደትና የፋሲካ በዓላት፥ የሚከበሩበትን ትክክለኛ ትርጉም ለማሳወቅ ምቹ ዕድል ይሰጣሉ። የልደትን ታሪክ ልጆች ትወና ሲሠሩና እና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን በድራማ መልክ ማቅረብ ሁልጊዜ ስሜትንና ጥያቄዎችን ይቀሰቅሳል።

## ለየት ያሉ ቡድኖችን ማገልገል

ስደተኞች፡- በአገርህ ሙስሊም ፈላሲዎች ወይም ስደተኞች ካሉ ክርስቲያናዊ ርኅራኄ አሳያቸው። ከቤተ ክርስቲያን ልብስ፥ ምግብ፥ ወዘተ. የሚያድሉ ቡድኖችን አደራጅ። ይህ ርዳታ ያለ አድልዎና ያለ ልዩነት በንጹሕ ክርስቲያናዊ ፍቅር መከፋፈል አለበት።

እስረኞች፡- በወህኒ የሚማቅቁ እስረኞች ርዳታ የሚያስፈልጋቸው ናቸው። የሙስሊም እስረኞችን አመኔታ ማትረፍ ከተቻለ፥ ለእውነተኛ መሰማትና ፍቅር ምላሽ ይሰጣሉ። ክርስቲያናዊ ሥነ -ጽሑፍና የመጽሐፍ ቅዱስ ተልእኮ ኮርሶችን ለምስክርነት መጠቀም ይቻላል።

የኤድስ ሰለባዎች፡- በዚህ አሰቃቂ መቅሰፍት ለሚሰቃዩ ክብካቤ በማድረግ ርኅራኄንና በጐነትን ለመግለጽ ክርስቲያኖች ዕድል አላቸው። የኤድስ ሰለባዎች ቤተሰቦችና ልጆችም እንዲህ ያለውን ክብካቤ በጽኑ ይፈልጋሉ።

## በጥልቀት የሚታሰብ

*** በአካባቢህ በግል ለሙስሊሞች ወንጌልን ለማድረስ የትኞቹ አሳቦች ናቸው ሊሳኩ የሚችሉት?

*** ከእነዚህ አገልግሎቶች በግልህ ልትሳተፍ የምትችለው በየትኞቹ ነው?

# ምዕ. 16 በመገናኛ ብዙኃን መጠቀም

በመገናኛ ብዙኃን መጠቀም የማኅበረሰብን ሰፊ ክፍል የመድረሻ ዋና ዘዴ ነው። የአሁኑ የዓለም ሁኔታ ሰዎች ከገጠር ወደ ታላላቅ ከተሞች እየፈለሱ ያሉበት እንደመሆኑ፥ የመገናኛ ብዙኃንን ጠቀሜታ በተለይ ያጕላዋል። ሙስሊሞችን ፊት ለፊት የመፋጠጡ ነገር ስለማይኖር በመገናኛዎች መጠቀም ስጋትን ይቀንሳል። በክርስቶስ ወንጌል ላይ ፍላጐት እንዳደረባቸው ሌሎች ሳያውቁባቸው ሬድዮ መስማት፥ ፊልም ማየት፥ ደብዳቤ ማግኘት፥ ወዘተ. ይችላሉ።

## 1. ሬድዮ መጠቀም፡-

ግጭት የማይፈጥር የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ማሰራጨት ይቻል እንደሆነ የአካባቢህን ሬድዮ ጣቢያ ቀርበህ ጠይቅ። የሬድዮ ጣቢያ ሠራተኞች አድማጮቻቸውን የሚያስደስቱ ፕሮግራሞችን ሁልጊዜ ይፈልጋሉ። የቀደምት አባቶች ታሪክና የነቢያት ጽሑፎች ሁሉንም ሙስሊሞች የሚያስደስቱ ናቸው። የአብርሃም፥ የያዕቆብ፥ የዮሴፍ፥ ወዘተ የመሳሰሉት የብሉይ ኪዳን ክፍሎች እና ከነቢያት የተውጣጡ ምንባቦች ለሬድዮ ተቀርጸው ሊወሰዱ ይችላሉ። ፕሮግራሙ «ከቀደምት አባቶችና ነቢያት ታሪክ» የሚል ተቀባይነት ያለው ስያሜ ሊሰጠው ይችላል። ምንም እንኳ አስተያየት መስጠት የማይፈቀድ ቢሆንም፥ አድማጮች ስለ መሚሑ መምጣት የተነገሩትን ትንቢቶች በመስማት የማወቅ ፍላጐታቸው ይነሣሣል።

እንደዚሁ ብዙ ባህሎች ጥንታዊ የምሳሌ አባባሎች ቅርስ ያሉአቸው ሲሆን ሰዎች ደግሞ ቅኔአዊ አገላለጾችን ያደንቃሉ። ስለዚህ መጽሐፈ ምሳሌ ለሬድዮ ንባብ ሌላው ምንጭ ነው።

ታሪኮችና ምሳሌዎች ከአዲስ ኪዳን ተወስደው ለዚህ ዓላማ ሊውሉ ይችላሉ። ጌታ ፈሪሳዊውና ቀራጩ ቤተ መቅደስ ሂደው ስለመጸለያቸው የተናገረው ታሪክ እንዴት በተዛምዶ ተቀንባብሮ እንደቀረበ ማንበቡን አስታውሳለሁ (ሉቃ. 18፡10)። ብዙ ቅመም ተጨምሮበትና በአስቂኝ መልክ ቢቀርብም ቅሉ ዋና አሳቡ የተጠቃለለው እንዲህ ነበር። በጸሎት ጊዜ ሁለት ሙስሊሞች ወደ መስጊድ ሄዱ። አንደኛው የአምልኮ ሥርዓቱን በመታጠብ፥ በድርጊትና በቃላት እያከናወነ እያለ አእምሮው ግን የጐረቤቱ ልጅ ስለሆነችው ወጣት ልጃገረድ በማሰላሰል በወሲባዊ ምኞት ይቃጠል ነበር። ሌላኛው ስለ ኃጢአቱ በጣም ስለተጨነቀ ሃይማኖታዊውን ሥነ ሥርዓት ለመፈጸም ተሳነውና ቀስ ብሎ ከሰው ዓይን በመሰወር ወደ መስጊዱ ጀርባ ሄዶ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው በልቡ አለቀሰ። ከእነዚህ ሁለቱ ሰዎች ጸሎት በእግዚአብሔር የተሰማው የየትኛው ነው?

እንዲህ ያለውን የቃል አቀራረብ በመከተል በሬድዮና በቴሌቪዥን ዝግጅት የሚያቀርቡ ቡድኖችን ማቀናጀት ይቻላል። ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን በመጠቀም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በአካባቢው ዜማ መዘመር ይቻላል።

## 2. ፊልሞች፥ ቪዲዮዎችና ፊልም ስትሪፖች:-

በአሁኑ ጊዜ ብዙ የክርስቲያን ፊልሞችና ቪዲዮዎች አሉ። ለምሳሌ ታላቁ ተልእኮ በተባለው ድርጅት የተዘጋጀው «ኢየሱስ» የሚለው ፊልም በብዙ ቋንቋዎች የተተረጐመ ሲሆን፥ በሙስሊም አገሮችም በሰፊው በአገልግሎት ላይ ውሏል። እንደዚሁም የሙዲ የሳንይስ ተቋም «ሐቅና እምነት» የተሰኙት ፊልሞችና የዶብሰን «በቤተሰብ ላይ ትኩረት» የተሰኙት ፊልሞች ለሙስሊሞች የሚያስደስቱ ሊሆኑ ይችላሉ። የዐረብኛ ፊልሞችንና ቪዲዮዎችን ከማጠቃለያው ዝርዝር ምንጮች ማግኘት ይቻላል።

እነዚህን ማሳየቱ ሥራንና ቅንጅትን የሚጠይቅ ቢሆንም፥ የተወሰኑ ሰዎችን ያቀፈ ቡድን ማደራጀት የሚከስ መንገድ ይሆናል። ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ሙስሊሞቹ ነፃነት ሊሰማቸው በሚችል ኪራይ ቤት ፊልሙን ማሳየቱ የተሻለ ነው። ሰፊ ክፍል የማይገኝ ከሆነ የሕንፃን ግድግዳ በመጠቀም ከቤት ውጪ ፊልሙን ማሳየት ይቻላል። በፊልሙ ቁም ነገር ላይ መንፈሳዊ ፍላጐት የሚያድርባቸውን ለመከታተል መንገድ መቀየስ አለበት።

ለአነስተኛ ቡድን የፊልም ስትሪፖች ለአጠቃቀም የቀለሉ ናቸው። «የደኑ ዶክተር» በተሰኘው ፊልም ስትሪፕ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ተምሳሌታዊ ገጸ ባሕርያት ተሰጥቷቸው በጥንቃቄ ተተርከዋል። በእነዚህ ተረቶች፥ ብዙ የዱር አራዊት የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በሚገልጽ ሁኔታ ልምምዳቸውን ይተርካሉ። እነዚህ አራዊት በሌሎች ሁኔታዎች በቀላሉ ሊያስቀይሙ የሚችሉ ንግግሮችን ይናገራሉ። ፊልም ስትሪፖችን በስላይድ ፕሮጀክተር አማካኝነት በቤት ውስጥ በግድግዳ ላይ ወይም ጨርቅ በማንጠልጠል ማሳየት ይቻላል።

## 3. የጋዜጣ ላይ ማስታወቂያዎች:-

በአካባቢው ጋዜጣ ላይ የተለያዩ ትምህርታዊ ጽሑፎችና የአንባቢዎችን ጥያቄና ዝንባሌ በማጤን የሚመጥኑ ሥነ-ጽሑፎች ማውጣት ይችላል። ጽሑፉ በጥንቃቄ የተመረጠና በሬድዮው ዝግጅት ላይ እንደተጠቀሰው ግጭት የማይፈጥር ቀለል ያለ መሆን ይገባዋል።

ሌላው ዘዴ ለጋዜጦችና ለመጽሔቶች አዘጋጆች ገንዘብ በመክፈል ለመረዳት የማይከብዱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ማብራሪያ ሳያክሉባቸው ማውጣት ነው።

በጋዜጦች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ኮርሶች ማስታወቂያዎችን ማውጣት ይቻላል። ብዙ ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን በግል ለማጥናት ስለሚፈልጉ ይህ ጥሩ መንገድ ይከፍትላቸዋል። ተማሪዎች ለጥያቄዎች መልሶቻቸውን በፖስታ ይልካሉ፤ ከዚያም የሚቀጥለው ትምህርት ይላክላቸዋል። ብዙውን ጊዜ ትምህርቶቹ ከተማሪዎቹ በኩል ጥያቄዎችን ያስነሣሉ፤ እናም ኮርሱን የሚያካሂዱት ክርስቲያኖች እንዲቀጥሉበት ይገፋፏቸዋል። ይህ ውጤታማ የወንጌል ስርጭት ዘዴ ሲሆን በበርካታ አገሮች ብዙ ሙስሊሞችን ወደ ደኅንነት የመራና የተለወጡትንም ወደ እድገት ያደረሰ ነው።

## 4. አሻንጉሊቶችን መጠቀም፡-

አሻንጉሊቶች ስሜት የሚቀሰቅሱ የማስተማሪያ ዘዴዎች ናቸው። የሌላውን ድምፅ አስመስለው የሚያወጡ አዝናኝ አሻንጉሊቶች ሰው ከሰው የማይለዋወጣቸውን ማናቸውንም ዓይነት አባባሎች መናገር ይችላሉ። ተረቶችንና ምሳሌዎችን 'መስማት እንዲሁም ድራማን መከታተል የተለመዱ እውነትን የማወቂያ መንገዶች ናቸው። በዚህ ነገር የጌታ ኢየሱስን ምሳሌ ተመልከት። ተከታዮቹ ላልሆኑት ፍቺውን ለማወቅ ማሰላሰልን በሚጠይቁ ምሳሌዎች ነበር ያስተማራቸው። ባህላዊ የመማማር ሂደት ተቀባይነት ባገኘባቸው አገሮች በዚህ ዘዴ መጠቀሙ አስፈላጊ ነው።

### በጥልቀት የሚታሰብ

*** ከመጋቢህና ከምእመናን ጋር በመሆን ለሙስሊም ወንጌል ስርጭት መገናኛዎችን ስለመጠቀም አሳብ ተለዋወጥ።

*** አንተና ወይም ቤተ ክርስቲያንህ በአካባቢያችሁ የትኛውን የመገናኛ ዘዴ መጠቀም ትችላላችሁ?

# ምዕራፍ 17 ሥነ -ጽሑፍን መጠቀም

ተስማሚ የሆነ ሥነ ጽሑፍ ለሙስሊም የወንጌል ስርጭት በጣም አስፈላጊ ነው። መንፈስ ቅዱስ ለደኅንነት በእግዚአብሔር ቃል እንደሚጠቀም ቅዱሳት መጻሕፍት ዘወትር ያሳስቡናል። «ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ» (1ኛ ጴጥ. 1፡23)። ሙስሊሞች ራሳቸው «ክርስቲያኖች በዱካቸው የሚተዉት መጽሐፍ ከሁሉም የበለጠ ኃይለኛ ነው፤ ሕይወትን የሚለውጥ መጽሐፍ ነው» ሲሉ እንሰማቸዋለን።

ትንንሽ ስጦታዎችን መስጠት በእስላማዊ ባህል በጣም ተቀባይነት ያለው ተግባር ስለሆነ፥ ሥነ ጽሑፍ ያለ ችግር ተቀባይነት አለው። አቀራረቡን

በተመለከተ በማስተዋል አከናውነው። አስገዳጅ ወይም ጠበኛ አትሁን። ተቀባይነት ማጣትንም ለመቀበል ተዘጋጅ። ሰውዬው በሚቀየምበትም ጊዜ በጥሩ መንፈስ ሆኖ ለማዘናናት መቻል ከፍተኛ ብቃት ነው። ሙስሊም ጓደኛህ የሚያሳያቸውን የውስጥ ስሜት ማሰብ አለብህ።

የእኔ ጓደኛ በአገራችን ትምህርቱን ከተከታተለ በኋላ ወደ አገሩ ከሚመለስ ወጣት ሰው አጠገብ በአውሮፕላን ውስጥ የመቀመጥ ዕድል ገጠመው። ወጣቱ ሰው አጥባቂ ሙስሊም ሲሆን የእስልምናን ታላቅነት እያወደሰ ሊከተሉት የሚገባ ሃይማኖት ስለመሆኑ በጠለቀ ስሜት ይናገር ነበር። ጓደኛዬ በጥንቃቄ ካዳመጠው በኋላ ክርስቲያናዊ ምስክርነቱን አጫወተው።

እንደኛቸውም ቢሆኑ ከራሳቸው ሃይማኖት የበላይነት ወደ ኋላ ፈቀቅ እንደማይሉ ከወዲሁ የታወቀ ነበር። ጓደኛዬ ሰውዬውን ዳግመኛ እንደማያገኘው በመገንዘብ አውሮፕላኑ ከማረፉ በፊት ሥነ -ጽሑፍ ለመስጠት ፈለገ። «አዲስ ኪዳን ብሰጥህ ትቀየም ይሆን?» በማለት ጠየቀው። ወጣቱ ሰውም «የለም፥ በእርግጥ አልቀየምም። ቢኖረኝ ደስ ይለኛል» በማለት መለሰለት።

ሂደቱ የሰመረ ውጤት የሚያስገኘው እንደሚከተለው ሲሆን ነው:-

. ወዳጃዊ አቀራረብ አሳይ፤

. ግልጽ ወደሆነ የአሳብ ልውውጥ ግባ፤

. የእምነትን ነገር በተመለከተ በልዩ ጥንቃቄ ተጫወት፤

. የእግዚአብሔርን ቃል ከሙስሊሙ ዘንድ ለመተው ሞክር።

. ለዚያ ለአገኘኸው ሰው ያለመታከት ጸልይለት።

## እግዚአብሔር እንዲጠቀምብህ የተዘጋጀህ ሁን

ሁልጊዜ ተስማሚ የሆኑ ትራክቶችና ትናንሽ መጻሕፍት አይለዩህ። ባገኘኸው አጋጣሚ ሁሉ ለማሰራጨት ተዘጋጅ። መንፈስ ቅዱስ በጉድለቱ ለሚወቅሰው ሰው ቃሉን ታደርስለት ዘንድ እንዲጠቀምብህ እግዚአብሔርን ጠይቀው። በጽሑፍ ያለ ቃል ሰውዬውን ከተገናኘህበት የመጀመሪያ ቀን በኋላ ለብዙ ጊዜ አብሮት ስለሚቆይ አንድ ቀን ሊጠቀምበት ይችላል። እኛንም በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር ሲጠቀምብን ትሕትና ባልተለየው መንፈስ ልንደሰት ይገባል።

ሙስሊሞችን ለማገልገል ሙሉ ሕይወቱን የሰጠና በዓረብኛ ቋንቋ የተካነ አንድ እንግሊዛዊ ሰው የመካከለኛ ምሥራቅ አገሮችን እንዲጐበኝ ዕቅድ ተያዘለት። ጉዞውን ሲጀምር አንድ የዓረብኛ አዲስ ኪዳን ከካቦርት ኪሱ ከተተና መጽሐፉን እግዚአብሔር ለሚፈልገው ሰው መስጠት እንዲችል ጌታ ይመራው ዘንድ ጸለየ።

ከጥቂት ሳምንታት ጉብኝትና ከበርካታ የአየር ጉዞዎች በኋላ ጉዳዩን ፈጽሜና ወደ ቤቱ መመለሻው ሆነ። ባልታወቁ ሁኔታዎች የበረራ ዕቅዱ ተስተጓጉለና በተለየ አቅጣጫ ወደ ቤቱ ለመመለስ ተገደደ። በአውሮፕላን ውስጥ ተቀምጦ የዓረብኛ ጋዜጣ እያነበበ እያለ ያች አዲስ ኪዳን በኪሱ መኖርዋን አስተዋለ። ከአጠገቡ የተቀመጠ አንድ የዓረብ ነጋዴ አውሮፓዊው የዓረብኛ ጋዜጣ በማንበቡ ስሜቱ ተቀሰቀሰበትና ንግግር ጀመሩ።

ትንሽ ቆይቶ መንፈሳዊ ጉዳዮችን መወያየት ጀመሩ። እንግሊዛዊው ሰውዬ የጉዞ ጓደኛውን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በበለጠ ለማንበብ ይፈልግ እንደሆነ ጠየቀውና ይዞት የነበረውን አዲስ ኪዳን አወጣለት። የዓረቡ ነጋዴም በደስታ እየፈነደቀ «ኢንጂልን (አዲስ ኪዳን) ቅጂ ለማግኘት አራት ዓመታት ሙሉ ስፈልግ ነበር፤ ታዲያ አንተ አሁን ሰጠኸኝ!» አለው። እግዚአብሔር ወደተዘጋጀና ወደሚሻ ልብ በመምራት የእንግሊዛዊውን ሰው ጸሎት በአስደናቂ ሁኔታ መለሰ።

ሙስሊሞች ልበ ደንዳኖች ስለሆኑ ወንጌልን አይሰሙም የሚለውን የአንዳንድ ሰዎች አነጋገር ሰምተህ ተስፋ አትቁረጥ። ልክ እንደዚህኛው ሰው ለእውነት የተራበ ልብ ያላቸው ብዙ ሙስሊሞች አሉ። ውጪአዊ የሃይማኖተኛነት ሽፋናቸውን እንደጠበቁ፥ በምሥጢር እውነትን ለማግኘት የሚተጉ ብዙ የአገሬ ሙስሊሞችን አውቃለሁ። ፈልገን እንድናገኛቸው እግዚአብሔር እንዲጠቀምብን እንጠይቀው።

## የሥነ-ጽሑፍ አመራረጥ

በመጀመሪያ ደረጃ በአነስተኛ፥ ይልቁንም በግል በሚሰጥ ሥነ-ጽሑፍ መጀመር ማለፊያ ነው። በኪስ ውስጥ ወይም በእጅ ቦርሣ ሊደበቅ በሚያስችል ሁኔታ የተዘጋጀ መሆን ይገባዋል። ለዚህ ዓላማ እንዲውል እኔና ባለቤቴ «ነቢያትና ቃሉ» የሚል አነስተኛ መጽሐፍ አዘጋጅተናል። የእግዚአብሔር ቃል «ብርሃን እንዲፈነጥቅ ማድረግ» በሚል መርህ ሥር፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተመርጠው ተሰብስበዋል። ዓላማዎቹ፥ ለአንባቢው መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነትን መረዳት ለመስጠት፥ ሙስሊሞች ብዙውን ጊዜ ስሕተቶች ናቸው የሚሏቸውን ነጥቦች ለመቋቋም እና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስብእናና ሥራ ላይ ያተኮሩ ናቸው። ዋናው ግቡም ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን ሳይሆን ተጨባጩን እውነት ለማሳየት ነው።

የመጽሐፉ አቀራረብና መልክ ባህላዊነትን የተላበሰ ስለሆነ፥ ስሜት የሚነካና በሙስሊሙ አእምሮ ቅዱስ መጽሐፍ የሚለውን አሳብ የሚያሳስብ ነው። በውስጡ ስለ ቁርዓን፥ መሐመድና እስልምና የሚጠቅስ ነገር የለውም። ርዕሱ ደግሞ ሆን ተብሎ ከታወቀው ወዳልታወቀው እንዲመራ ተደርጎ የተመረጠ ነው።

እጥር ምጥን ባለ መልኩም ቢሆን የመጽሐፉ ይዘት የሚያወሳው እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሁሉ ስላለው ፍቅር ነው። መጽሐፉ ፍጥረት፥ አዳምና ሔዋን፥ ቅዱሳን አባቶችና ነቢያትን በመሳሰሉ በሙስሊሞች ዘንድ በታወቁ ሰዎችና ድርጊቶች ይጀምራል። በሙስሊሞች አስተሳሰብ የትውልድ ሐረግ ጉዳይ ትልቅ ስፍራ ስላለው፥ የክርስቶስ የትውልድ ሐረግ የብሉይ ኪዳን ክፍሎችን እንዲያያይዝ ተደርጓል።

ይህ ደግሞ በበኩሉ በወንጌል ወደተዘከረው የክርስቶስ ሕይወትና ሥራ ብሎም በመልእክቶች ወደተገለጸው ሞቱና ትንሣኤው አስፈላጊነት ይመራል። ስለ እግዚአብሔር ፍርድና የሰይጣን ኃይል ሙስሊሙ ስላለው ግንዛቤ ማጠናከሪያ ይሰጥና፤ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት የመናፍስትን ዓለም እንደረታና ኃጢአተኞችን እንዳዳነም ያሳያል። የክርስቶስ ሞት፥ ትንሣኤው፥ መለኮትነቱ፥ በራሱ ሥልጣን ታምራትን የማድረግ ኃይሉ፥ የመሳሰሉ በሙስሊሞች የተዛባ አመለካከት ላይ የሚያተኩሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በመጽሐፉ ዓውደ ንባብ ውስጥ በጥንቃቄ ተጠናቅረዋል።

ተነባቢነትን ለማቅለል ምዕራፎችና ቁጥሮች ከመጽሐፉ ተወግደዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎች በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ የተጠቀሱ ሲሆን ለዚያውም በምዕራፍ ብቻ ነው። ለዚህም ምክንያቱ አንባቢው ለማጣቀስ ከፈለገ የዚያን መጽሐፍ ክፍል ዓውደ ንባብ እንዲያነበው ለማድረግ ነው። «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው ስም ለሙስሊሞች ዕንቅፋት ስለሆነ፥ መጀመሪያ በታየበት ገጽ ላይ የግርጌ ማስታወሻ ተሰጥቷል። የግርጌ ማስታወሻው፦

> «የእግዚአብሔር ልጅ» - የመሢሑ ስም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚባል የገለጸው መልአኩ ገብርኤል ነው። ይህ ስም እግዚአብሔር ከሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳደረገ አያመለክትም። እንዲህ ያለውን አስነዋሪ አሳብ እግዚአብሔር ከአእምሮአችን ያስወግደው። የስሙ ትርጓሜ መሢሑ ኢየሱስ የማይታየው እግዚአብሔር የሚታይ መገለጫ ማለት ነው።

ይዘቱንና የትረካውን አወራረድ ለመረዳት እንዲረዳ ርዕሶች በጥቅም ላይ ውለዋል። በተቀረ ጽሑፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ብቻ ነው። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል ለአንባቢዎች እንዲተረጎምና እንዲጠቀምባቸው በማለት ሌላ ማብራሪያ አልታከለበትም።

ይህ መጽሐፍ ያበረክታል ተብሎ የታለመባቸው ጥቅሞች፥ ከእርስ በርስ ውይይት በኋላ ለሌሎች ሊተላለፍ፥ ለሬድዮ ፕሮግራሞች በተከታታይነት ሊቀርብ፥ ቤት ለቤት ሊከፋፈል፥ በቀላሉም በፖስታ ቤት ለመላክ በሚያስችል ሁኔታ መዘጋጀቱ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ መጽሐፉ በዘጠኝ ቋንቋዎች ማለትም በእንግሊዘኛ፥ በዓረብኛ (ቫን ዳይክ)፥ በዓረብኛ (ሕያው መጽሐፍ ቅዱስ)፥

በፈረንሣይኛ፥ በቱርክኛ፥ በቱርክኛ (ሲሪልክ)፥ በሐውሳ፥ በኢንዶኔዢይኛ፥ በታታር፥ በቻይንኛ (ባህላዊ ጽሑፍ) ተተርጉሞ ይገኛል። በሌሎች በርካታ ቋንቋዎችም በመተርጐም ሂደት ላይ ነው። መጽሐፉ በዩ.ኤስ.ኤ. (The Bible League, USA ) ወይም በአገርህ ከሚገኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ሊግ ቢሮ ሊገኝ ይችላል። (አባሪ«ለ»ን ተመልከት።)

የ«ቅዱሳት መጻሕፍት አዳይ ሚሲዮን» (The Scripture Gift Mission) የተባለውም ድርጅት ተስማሚ ሥነ -ጽሑፎችን ለማግኘት ማለፊያ ምንጭ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ብቻ የያዙ በተለያዩ ርዕሶችና በተለያዩ ቋንቋዎች የተጻፉ ትራክቶችና ትናንሽ መጻሕፍት አሏቸው። እነዚህን ሥነ -ጽሑፎች መስጠቱ እየሠመረ ሲመጣ፥ ወንጌላትን፥ አዲስ ኪዳኖችንና መጽሐፍ ቅዱሶችን ወደ መስጠቱ ደረጃ መድረስ ይቻላል። እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራትና ሌሎች መጽሐፍ ቅዱስን በማሰራጨት ሥራ ላይ ከተሰማሩ ድርጅቶች ዘንድ በተለያዩ ቋንቋዎች ይገኛሉ። (አባሪ «ለ»ን ተመልከት።)

## ክርስቲያናዊ ሥነ -ጽሑፎች እንዲገኙ ማድረግ

የሚቻል ከሆነ በሙያተኞችና በመንግሥት ቢሮዎች ውስጥ በሚገኙ የእንግዳ መቀበያዎች ወይም በትምህርት ቤቶች፥ በንባብ ቤቶችና በአብያተ መጻሕፍት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱሶችን ለማስቀመጥ ፈቃድ ጠይቅ።

በአሁኑ ጊዜ በኪራይ የሚገኙ ካሴቶችንና ቪዲዮዎችን የመሳሰሉ ዓይነት ሰፊ የሆኑ ማራኪ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች አሉ። (Language Recordings International) የተሰኘው ድርጅት በብዙ ቋንቋዎች የተዘጋጁ የወንጌል ካሴቶች አሉት። እነዚህ ደግሞ ተነጥለው ለሚኖሩ ጐሣዎች፥ ሴቶችና አረጋውያንን ለመሳሰሉና የማንበብ ችሎታ ላልታደሉ ሰዎች በተለየ ሁኔታ ይጠቅማሉ። እንደዚሁም ኤል.አር. (L.R.) («ዓለም አቀፍ የቋንቋ ቀረጻ») «እይ፥ ስማ፥ በሕይወትም ኑር» (Look, Listen, live) በሚል ርእስ በተከታታይነት የሚዘጋጁና እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ማስተማሪያዎች አሉት። ታዲያ እነዚህ በሥዕል ብቻ የተዘጋጁ መጻሕፍት ሲሆኑ፥ በድምፅ የሚገልጹ ካሴቶች በበርካታ ቋንቋዎች ተዘጋጅተውላቸዋል። (አድራሻዎቹን ለማግኘት አባሪ «ለ»ን ተመልከት።)

ሥነ -ጽሑፍን በደብዳቤ ማሰራጨቱ የፖስታ አገልግሎት በሚገኙባቸው ከተሞች የሚኖሩትን መጠነ-ሰፊ ተደራሲያን ለመድረስ አንዱ መንገድ ነው። በደብዳቤ ውስጥ ምላሽ መስጫ ወረቀት አብሮ ይላክና ፍላጐት ያላቸውን ሰዎች ለመከታተል ያገለግላል። እንዲህ ያለውን ፐሮግራም በሥራ ለመተርጐም የሚያስፈልግ ዝርዝር ጉዳይ በአባሪ "ሠ" ተጠቅሷል።

ሙስሊሞችን ስለመድረስ የሰጠኋቸው እነዚህ ምክሮች ጠቃሚ እንደሚሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ። ምናልባት ከእነዚህ መንገዶች የትኛውም ባለህበት ሁኔታ

ውስጥ ሊተገበር የማይችል ይሆናል፤ ዳሩ ግን በአገርህ ላሉት ሙስሊሞች ወንጌልን ለማድረስ የግል የፈጠራ መንገዶችን እንድትቃኝ ያነቃቁህ ዘንድ እጸልያለሁ። እንዲመራህ የእግዚአብሔርን ፊት ፈልግ። የእግዚአብሔርን ቃል በሙስሊሙ እጅ ውስጥ ማስገባቱ ራሱ ከፍተኛ እርምጃ ነው።

## በጥልቀት የሚታሰብ

*** ቤተ ክርስቲያንህ ለአባላት የምስክርነት አገልግሎት የሚውል የሥነ-ጽሑፍ ማስቀመጫ የሆነ የትራክት ሣጥን እንድታዘጋጅ ገፋፋ።

*** ለሙስሊሞች ተስማሚ የሚሆን ሥነ -ጽሑፍና ቅዱሳት መጻሕፍት የሚገኙበትን ምንጭ አግኝ።

# የመሠረተ አሳቦች ማጠቃለያ

የሚከተለው ብዙውን ጊዜ ሙስሊሞችን የመድረስ «አሥርቱ ትእዛዛት» የሚል መጠሪያ የተሰጠውና ለሙስሊሞች ወንጌልን የማስረጫ መሠረተ አሳቦችን ያጠቃለለ መመሪያ ነው። በመጽሐፉ ለተሰጡት አሳቦች አስታዋሽ በመሆንም ያገለግላል።

1. በእግዚአብሔር ቃል ተጠቀም። ሙስሊሞች እንደ ሙሴ ሕግ፥ መዝሙረ ዳዊት፥ ወንጌላት እና ቁርዓን የመሳሰሉትን ቅዱሳት መጻሕፍት ያከብራሉ። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ እንዲናገር አድርግ።

2. ያለማቋረጥ ጸልይ። ወንዶችና ሴቶችን ለክርስቶስ ሊማርክ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ነው። ቃሉን በምታቀርብበት ጊዜ የእርሱን ምሪትና ኃይል በመሻት ይሁን።

3. እውነተኛ ወዳጅ ሁን። ወዳጃዊ ሰላምታ መለዋወጥ የመጀመሪያው እርምጃ ነው። በእርግጥም የምታስብላቸው ከሆነ ሙስሊሞችን ወደ ቤትህ በመጋበዝ፥ ጊዜህን በማካፈልና ችግራቸውን በመረዳት ተቆርቋሪነትህን አሳያቸው

4. ለማሰላሰል የሚጋብዙ ጥያቄዎችን ጠይቅ። «ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለህ?» «የኃጢአት ይቅርታ አግኝተሃልን?» «እግዚአብሔር ጸሎቶችህን ይመልሳልን?» «መንግሥተ ሰማይ እገባለሁ ብለህ ትገምታለህን?» ይህን የመሳሰሉት ነጥቦች በሙስሊሙ ሕይወት ውስጥ ተቀዳሚ ሚና ስለሚኖራቸው በጥያቄ መልክ ማንሳትህ ተቆርቋሪነትህን ያሳይልሃል።

5. በጥሞና አዳምጥ። ጥያቄ ከጠየቅህ መልሱንም በትሕትና አዳምጥ። ደግሞም ስለ ሙስሊሞች የአስተሳሰብ ዘይቤ የበለጠ መማር ስለምትችል በተሻለ ሁኔታ ልትወዳጃቸው ትችላለህ።

6. እምነትህን በግልጽ ተናገር። የምታምንበትን ትምህርት የሚደግፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በማሳየት በግልጽና ያለአንዳች ቅሬታ ተናገር። በዚህ መንገድ የአስተምህሮትን ኃላፊነት በተገቢ ቦታው ማለትም በእግዚአብሔር ቃል ላይ ታኖራለህ።

7. ምክንያት አቅርብ እንጂ አትከራከር። መከራከር አንድን ነጥብ ለመርታት ቢያስችልም ተደማጭነትን ግን ያሳጣል። ብዙ ግለት ቢያስከትልም ምንም ብርሃን ግን አያስገኝም። መከራከር አልፎ አልፎ እንኳ የሚያስገኘው ነገር ምንም የለም፤ ደግሞም የአንተንም ሆነ የወንጌልን ቃል እንዳይቀበል የሌላውን አእምሮ ሊዘጋ ይችላል።

8. በምንም ዓይነት መሐመድን ወይም ቁርዓንን አታጉድፍ። ይህ ማለት፥ ለክርስቶስና ለመጽሐፍ ቅዱስ ከበሬታ መንፈግ አንተን የሚያስቀይምህን ያህል ሙስሊሙን ያስቀይመዋል ማለት ነው።

9. ባህላቸውንና በጣም የሚነኩበትን ነገር አክብርላቸው። መጽሐፍ ቅዱስን (የተቀደሰን መጽሐፍ) በወለል ላይ አታስቀምጥ፤ ወይም በተቀደሱ ጉዳዮቻቸው ማለትም በጾም፥ በጸሎት እና በአላህ ላይ አትቀልድ። መስተንግዶ አትንፈጋቸው፤ የሚያስቀይማቸውን የምግብ ዓይነት ለምሳሌ የአሳማ ሥጋና አልኮልን አታቅርብላቸው። አለባበስህ አግባብ ያለው ይሁን፤ ደግሞ ከተቃራኒ ፆታ ጋር በጣም ልቅ ሆነህ አትቀረብ።

10. በትዕግሥት ፅና። ክርስቶስ ስለራሱ የሚናገራቸው ነገሮች በሚገጥሟቸው ጊዜ ሙስሊሞች ብዙ ማሰላሰል ይጠይቃቸዋል። ስሕተታቸውን እንዲቀበሉ በማስጨነቅ የሚገቡበትን አታሳጣቸው። በእግዚአብሔር ምቹ ጊዜ ቃሉ ሥራውን እንደሚሠራ በማመን በመረጋጋት ጠብቅ።

ማስታወሻ:- ከሙስሊሞች ጋር የምታደርገው ወዳጅነት ተገቢውን አቅጣጫ የያዘ እንዲሆንልህ እነዚህን አሥር ነጥቦች በማዘውተር ደጋግመህ አንብባቸው።

## መደምደሚያ

የሙስሊም ወንጌል ስርጭት ሊደረግ እንደሚችልና አንተም ልታካሂደው እንደምትችል እነዚህ ልምምዶችና ትምህርቶች ያለጥርጥር ያበረታቱሃል ብዬ አምናለሁ። እርግጥ ተልእኮው ቀላል አይደለም፤ ደግሞም በገዛ ኃይልህ የምታደርገውም አይደለም። የሙስሊሙ ዓለም በወንጌል ሊደረስ የሚችለው ማንኛውም ክርስቲያን፥ የእርሱ ወይም የእርሷ ሥራ የፈለገውን ዓይነት ቢሆንም በዕለታዊ ግንኙነታቸው ለሚያጋጥሟቸው ሙስሊሞች ወንጌልን ሲነግሯቸው ብቻ ነው። በዚህ ዓለም ያሉትን አንድ ቢሊዮን ሙስሊሞች በእስልምና ጠበብት በሆኑ በጣት በሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ ከቶውንም ማዳረስ አይቻልም።

በወንጌል ስርጭትህ ወቅት በግብና በፍላጐት መካከል ያለውን ልዩነት ልብ ማለት ጠቃሚ ነው። ግቦች ልንፈጽማቸው የምንችላቸውና ኃላፊነታችንም የሆኑ ነገሮች ናቸው። ፍላጐቶች ደግሞ ተፈጽመው ለማየት የምንጓጓላቸው፥ ነገር ግን የሌሎች ሰዎች ፈቃድና ድርጊት ስለሚካተቱባቸው ከቁጥጥራችን ውጭ የሆኑ ነገሮች ናቸው። የእኛ ግብ ሙስሊሞችን መወዳጀትና መመስከር፥ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ማንነትና ሥራ እውነቱን ማካፈል ነው። አንዳንዶቹ ግብዣችንን ሲቀበሉ ሌሎቹ ግን አዎንታዊ ምላሽ አይሰጡም፤ ነገር ግን እኛ ስለ ደኅንነታቸው ኃላፊነት የለብንም - እግዚአብሔር እንጂ። የእኛ ፍላጐት ሙስሊሞች ንስሐ ገብተው ወንጌልን እንዲያምኑ ነው። ስለዚህ ወሳኙ መሠረተ አሳብ ወደ ግብ ለመድረስ መጣር አለብህ የሚል ሲሆን፥ ፍላጐቶች እንዲፈጸሙ ደግሞ ጸልይ የሚል ነው። በእርግጥ፥ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ማናቸውም የወንጌል ስርጭት ሙከራችን በጸሎት የታገዘ መሆን አለበት።

የትኛውም የወንጌል ስርጭት ቢሆን ከባድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ደጋግሞ የውጊያን ተምሳሌት ይጠቀማል። ስለዚህ በምስክርነትህ ላይ ጥብቅ ተቃውሞ ተነሥቶ ችግሮችን፥ መከራዎችንና አደጋዎችን እንኳ ቢያስከትልብህ አትደነቅ። ውጊያ ማለት እንዲህ ዓይነት ነው። ነገር ግን እነዚህ «የብርቱው ሰው»ማለትም የሰይጣን ዕውር ምርኮኞች ወንጌልን መስማት አለባቸው። ማን ይንገራቸው? በጦርነት ወደተበጣጠቀች አገር ተመልሰው በሙስሊሞች መካከል ለመሥራት ስለቆረጡ አንዲት አረጋዊት ሴት ስሰማ በጣም ስሜቴ ተነካ። ሴትዮዋ ስለሚገጥማቸው አደጋ በተነገራቸው ጊዜ፥ «በጌታችን ድል ሐሴት ለማድረግ የዘላለም ዘመን በእጄ ነው፤ ስለዚህ በእርሱ ውጊያ ለዚህች ኢሚንት ጊዜ መሰለፍን ከምንም አልቆጥረውም» ብለዋል።

ዛሬ ለጌታ እንዲህ በአደጋ ውስጥ ደፍረው የሚገቡ የት አሉ? ለጊዜያዊ ጥቅም ሳይሆን ለዘላለማዊ ክብር የሚኖሩ ወጣቶች የት ናቸው? በዘመናችን «በእምነት» ምርኮ የሚበዘበዙ የዕብራውያን ምዕራፍ 11 የእምነት ጀግኖች ተከታይ የሚሆኑ የት አሉ? ሰማኒያ አምስት ዓመት ሆኖት ከባዱን ሥራ ለመሥራት ከቆረጠው ከካሌብ ጐን የሚሰለፉ የት ናቸው?

የአዳኙ መልእክት ሁልጊዜ በተደጋጋሚ ተቀባይነት የሚያጣ ከሆነ በሕዝቅኤል 33፡1-6 በተጻፈ ቃል ተጽናና። ሕዝቅኤል ከተማን እንደሚጠብቅ ዘበኛ ሆኖ በንጽጽር ቀርቧል። ጠባቂው ወይም ዘበኛው አደጋ አይቶ ሕዝቡን ቢያስጠነቅቅ ሕዝቡ ግን ማስጠንቀቂያውን ቸል በማለት ቢሞቱ ደማቸው በገዛ ራሳቸው ላይ ነው። ይሁንና ጠባቂው የማስጠንቀቅ ግዴታውን ቸል ቢልና በእርሱ ቸልተኝነት የተነሣ ሕዝቡ ቢሞቱ እግዚአብሔር ቀጥሎ ያለውን ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡- «... ደሙን (ደማቸውን) ግን ከጉበኛው እጅ

እፈልጋለሁ» (ቁ. 6)። እግዚአብሔር ሁላችንንም የእርሱ ዘበኞች አድርጎናል። ታማኝነታችንን በማጽናት እንሥራ።

የሙስሊም ወንጌል ስርጭት ከባድ ነው፤ ነገር ግን በእምነት መቀጠል አለብን። እንደ መስካሪነታችን የምንሠራው ሥራ ልክ በመንገድ እንደተተከለ ምልክት ነው። መንገደኞች የፈለጋቸውን አቅጣጫ ቢከተሉም የመንገድ ምልክቱ ግን አሁንም ማመልከቱን ይቀጥላል። ሥራችን የዓለም አዳኝ ወደ ሆነው ወደ ጌታ ኢየሱስ ማመልከት ነው። በእርሱ ኃይል እምነትህን በትሕትናና ከልብ በመነጨ ፍቅር አካፍል። ይህ አንድ ለማኝ ለሌላው ለማኝ ምግብ የሚያገኝበትን ዘዴ እንደሚያሳየው ዓይነት ሁኔታ ነው።

ከውጊያው መራራነት የተነሣ ለመተው በምንፈተንበት ወቅት ደቀ መዛሙርት የገጠማቸው ዓይነት አማራጭ የማጣት ነገር ይገጥመናል። «ኢየሱስም ለአሥራ ሁለቱ:- እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን?» አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስ ግን «ጌታ ሆይ፥ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ» (ዮሐ. 6:67፥ 68) በማለት መለሰ።

«አምላካችንስ የደኅንነት አምላክ ነው» [መዝ. (68):20] የሚለውን ከቶ አትዘንጋ። በጥንት ዘመን በነቢያቱ ታምራትን አድርጓል። ከሁሉም በላይ እርሱ እግዚአብሔርና የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነው። ጌታ ለክብሩ ይጠቀምብህ።

## በጥልቀት የሚታሰብ

*** ሙስሊሞችን በወንጌል ለመድረስ የምትነድፋቸው ግቦች የትኞቹ ናቸው?

*** በወንጌል ስርጭትህ እግዚአብሔር እንዲፈጽምልህ የምትጠይቃቸው ትክክለኛ የሆኑ ፍላጎቶች ምንድን ናቸው?

# A. Recommended Reading

## Basic Helps in Muslim Outreach

**Your Muslim Guest**, published by Fellowship of Faith For Muslims, P.O.Box 65214, Toronto, Ont. M4k 3z2. A practical guide for Christians. FFM has a wide range of literature about Islam.

**The Fortress And The Fire**, by Phil Parshall, Bombay: Gospel Literature Service, 1975. An excellent, readable book for a basic grasp of Islam.

**A Christian Response to Islam**, by William M Miller, Wheaton, Il: Tyndale House, 1976. A presentation of Islam by a missionary in Iran for forty-three years, contains testimonies of conversion of seven Muslims.

**Share Your faith With A Muslim**, by C R Marsh, Chicago, IL: Moody Press. Practial approach to witnessing by a man with forty years experience in Muslim evangelism.

**But I Love Him . . .** , by Harry Young. Available for WEC INTERNATIONAL, Bulstrode, Gerrards Cross, Bucks SL9 8SZ, England. A pamphlet cautioning Christians girls about emotional involvement with Muslims.

## Bigoraphies of Converted Muslims

**I Dared To Call Him Father**, by B Sheiks, Waco, TX.: Word, 1978. Testimony of a high born Pakistani lady who found Christ. (የአበቦቹ እመቤት፥ቢልቂስ ሼይክ፥ ትርጉም ግርማዊ፥ የመጨረሻዋ ሰዓትአሳታሚዎች ማኅበር፥ ህዳር 1998 ዓ.ም.)

**Captive Of The Christ**, by Steven Masood, Bomay: Gospel Literature Service, 1984. A gripping testimony of the conversion and persecution of a Pakistani.

**Jesus More Than A Prophet** - Fifteen Muslims Find Forgiveness, Release and a New life, by R W F Wootton (ed.), Leicester: Intervarsity Press, 1982. Testimonies of Muslims from different backgrounds who found new life in Christ.

## Advanced Reading About Islam

**Islam And Christian Witness**, by M Goldsmith, England:STL Books, 1982. Clear presentation of Muslims today, and Christian witness among them.

**The Bible And Islam; Sharing God's Word With A Muslim**, by Bassam M Madany, The Back To God Hour, 6555 W. College Dr., Palos Heights, IL. 60463. Guide book by an Arab with many years experience in gospel broadcasting into the Middle East.

**Sharing Your Faith With A Muslim**, by Abdiyah Akbar Abdul-Haqq, Minn.MI.: Bethany Fellowship, 1980. An authoritative book by an evangelist with Billy Graham team.

**Christians Ask Muslims; and Christians Answer Muslims**, by Gerhard Nehls, South Africa: SIM/LIFE CHALLENGE, 1988. Two books dealing with differences in Islam and Christianity. (ለሙስሊሞች ጥያቄዎች የክርስቲያኖች መልሶች፥ በጌርሃርድ ኔልስ፥ አዲስ አበባ)

**Christians Reply to Muslim Objections**, by Rev W St.Clair Tisdall, P O Box 13, A9503 Villach, Austria: Light of Life, 1980.

**The Person of Chrsit in The Gospel and The Koran**, by Abd Al-Fadi, P o Box 66, CH8486 Rikon, Switzland: The Good Way.

**The Meaning of The Glorious Koran**, by M Pickthall, London: Allen & Unwin, 1976. English paraphrase of the Arabic text.

(Note: Some of this information will need to be altered for various regions of the world.)

# B. Sources of Material for Muslims

## BIBLE DISTRIBUTORS:

**The Bible League**, 16801 Van Dam Rd., South Holland, IL 60473, USA.

**The Bible League**, 10 Carnforth Rd., Toronto , ON M4A 2SA CANADA.

**The Bible League**, P O Box 67092, Nairobi, KENYA.

(THE PROPHETS AND THE WORD, available in many languages from The Bible League)

## BIBLE SOCIETIES:

American Bible Society, 1865 Broadway, NY 10023, USA.

United Bible Societies - General Office, Reading Bridge House, Reading RGI - \ 8PJ, ENG.
P O BOX 42726, Nairobi, KENYA.

## SCRIPTURE GIFT MISSION:

P.O.BOX 195575, Winter Springs, FL 32719-5575, USA.

Radstock House, 3 Eccleston St., London, SW1W 9LZ, ENGLAND.

## LANGUAGE RECORDING INT.:

PMB 19, Castle Hill, NSW 2154, AUSTRALIA.

P.O. BOX 62, Gloucester, GL1 5SE, England.

Gospel Recordings Int., 122 Glendale Blve, Los angeles, CA 90026.

P O BOX 21244, Nairobi, KENYA.

## 'JUNGLE DOCTOR' FILM STRIPS & COMICS:

Paul White productions, 6 Newark Cres., Lindfield, NSW 2070, Australia.

## MATERIAL AVAILABLE in AFRICA

Challenge Publications, P.M.B. 2010, Jos, NIGERIA.

CHASIM, c/o SIM, B.P. 438, Conakry, GUINEA.

JESUS to the MUSLIMS, P O BOX 1804, Benoni 1500 RSA.

(Many books, tracts, audio-cassettes)

Life Challenge (Africa), P O BOX 1803 Southdale 2135, Johannesburg, RSA.

(B.C.C. and booklets for Muslims)

Life Ministries, P O BOX 21417, Nairobi, KENYA.

(GENESIS film & JESUS film in a number of languages)

Light of Life, P O BOX 83070, Mombasa, KENYA.

('One God - One Way, B.C.C.)

Njia Ya Uzima, P O BOX 21012, Nairobi, KENYA.
CH-8486 Rikon, P O BOX 66, SWITZERLAND.

(Many books and tracts in several languages)

People of God, P O BOX 16406, Nairobi, KENYA.
(Series of four study booklets in several African languages)

## LITERATURE & VIDEOS in ARABIC:

Middle East Christian Outreach, P O BOX 662, Larnaca, CYPRUS, CYPRUS.

Middle East Media, P O BOX 631, Worthing, West Sussex, BN13 1AP ENGLAND.

# አባሪ «ሐ» ሥቃይና ስደት

በዚህ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተጻራሪ በሆነ ዓለም ውስጥ ሥቃይና ስደት ለክርስቲያኖች በተለይም በሙስሊም የወንጌል ስርጭት ለተሰማሩት እንዴ የተወሰነላቸው ዕድል ፋንታቸው ነው። ስለዚህ በእነዚህ ክርስቲያናዊ የሕይወት ገጽታዎች ላይ ያለንን መረዳትና ዝንባሌ መመርመር ያሻናል። ለመሆኑ ፈተና በሚገጥመን ወቅት እግዚአብሔር የተወን ወይም እየቀጣን ያለ መስሎ ይሰማን ይሆን? በዚህ ጉዳይ ላይ መጻፉ ባያስደስትም፥ ዳሩ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚታይ ዋና አሳብ ስለሆነ መወሳት እንደሚገባው አስባለሁ። ሥቃይና ስደት፥ በሽታ፥ የሚወዱት ሰው በሞት መለየት፥ መገፋት፥ ድህነት፥ የሸምቅ ጥቃቶች፥ የጐሣ ጥላቻ፥ አብዮት፥ የመሳሰሉትን መልኮች ሊይዙ ይችላሉ። ልክ እንደዚሁ ሁሉ እንደ ረሃብ፥ ቸነፈር፥ የተባይ ወረራ፥ የውኃ መጥለቅለቅ፥ የምድር መናወጥ የመሳሰሉ የተፈጥሮ አደጋዎችም አሉ።

ሥቃይን በሁለት ርዕሶች እንመልከተው። በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ሰው በመሆናችን የተነሣ በስደት የሚመጣ ሥቃይ ይሆናል። ሁለተኛው ሕዝቡ መንፈሳዊ እድገትን ያገኙ ዘንድ እግዚአብሔር በሥቃይ ውስጥ እንዲያልፉ የሚፈቅደው ነው። እነዚህ በጣም ሰፊ የሆኑ የሚደራረቡ ርዕሶች ናቸው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ለመመርመር በምናተኩርበት ጊዜ ጠቃሚ ርዕሶች ሆነው እናገኛቸዋለን።

## እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ በስደት ውስጥ መሠቃየት

በቃሉ ውስጥ ይህ ነገር በተደጋጋሚ ይታያል። ከዚህ ቀጥሎ ከዮሐ. 15:18 እስከ 16:4 ውስጥ ያለው ፍሬ አሳብ ቀርቧል። ጌታ ኢየሱስ ሲያስጠነቅቅ፥

«ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደጠላኝ እወቁ። ... ባርያ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስቡ። እኔን አሳደውኝ እንደ ሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዱአችኋል፤ ... .. ከዚህ በላይ ደግሞ የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል» ብሏል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በግልጽ ተናግሯል። ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ታማኞች ከሆንን እርሱ የሄደበትን መንገድ እንሄዳለን። ከእግዚአብሔር ጋር ጠላት በሆነ ዓለም ውስጥ የሚኖር የተቀደሰ ሕይወት፥ ጥላቻን፥ አለመግባባትንና ስደትን ያስነሣል። እንዲያውም በሰማዕትነት መሞትን እስከማስከተል ሊደርስ ይችላል።

የዚህ እውነት ግልጽ ምሳሌ የሆኑትን የሐዋርያው ጳውሎስ ጉልህ ልምምዶች ተመልከት። አብያተ ክርስቲያናት እንዴት መመላለስ እንደሚገባቸው ማስተማር ብቻ ሳይሆን በትክክል «ወንድሞች ሆይ እኔን የምትመስሉ ሁኑ» (ፊልጵ. 3፡17)ይላል። ከዚህ የተነሣ የእርሱን መንፈሳዊ ሕይወት ውጤቱን ተመልከት። በኢየሩሳሌም የተከበረ የአይሁድ መሪ ከመሆን በክርስቲያንነቱ የተጠላና የተዋረደ ተደረገ። ራሱን «... የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጉድፍ ...» (1ኛ ቆሮ. 4፡13) በማለት ገልጿል። እንደ አንድ የእግዚአብሔር ሰው ሆኖ በስደት የደረሰበትን ሥቃይ ስንመለከት ግራ የሚያጋባ ነው። ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የማይገባ ትችት በደረሰበት ጊዜ ለክርስቶስ በሚሰጠው አገልግሎቱ ውስጥ የገጠሙትን ሥቃዮች ይዘረዝራል። እንዴት ያሉ የፈተናና የመከራ ዝክረ ዝርዝሮች ናቸው! በ2ኛ ቆሮ. 11፡22-28 ተዘግበው ይገኛሉ።

የዛሬውም ሁኔታ የተለየ መልክ የለውም። በጽኑው አቋሙ ምክንያት ሞት የተፈረደበትና በተገለለ ስፍራ ለዘጠኝ ዓመታት የታሰረ ሰው ከተናገረው የተወሰደ ፍሬ አሳብ ይኸውላችሁ። በእስልምና አገዛዝ ሥር ባለ አንድ አገር በሙስሊም ፍርድ ቤት መከላከያ እንዲያቀርብ ተደረገ። ጌታ ኢየሱስ እርሱን ለማዳን ስላደረገው አስደናቂ ነገር ከተረከ በኋላ እንዲህ በማለት ቀጠለ፡-

> «ለደግነቱ ምላሽ፥ ራሴን እንድክድና ራሴን የሰጠሁ ተከታዩ እሆን ዘንድ ጠየቀኝ። ሥጋዬን እንኳ ቢገድሉት ሰዎችን እንዳልፈራ ነገር ግን የምሕረትንና የርኅራኄን አክሊል ባቀዳጀኝ ደግሞም ለወዳጆቹ ታላቅ ጠባቂና ዕድል ፈንታቸው በሆነው በሕይወት ፈጣሪ ላይ እታመንበት ዘንድ ጠየቀኝ።

የኢዮብ አምላክ ትዕግሥቴንና ታማኝነቴን ያጠነክር ዘንድ እምነቴንና ውሳኔዬን ፈትኖአቸዋል። በእነዚህ ዘጠኝ ዓመታት ከተባረከ ስሙ ከለላ ሥር በመሆን ልቤን በመመርመርና ራሴን በማዋረድ ጊዜዬን በጸሎትና ቃሉን በማጥናት እንዳሳልፍና ጌታዬን በማወቅ እንዳድግ ከኃላፊነቶቼ ሁሉ ነፃ

አድርጎኛል። ለዚህ ልዩ ዕድል ጌታን አከብረዋለሁ። በእስራቴ እግዚአብሔር ቦታ ሰጠኝ፤ ከባዶቹ መከራዎቼም ፈውስን አስገኙልኝ፤ ደግሞም በቸርነቱ ነፍሴን አደሳት። እግዚአብሔር ለሚፈሩት ያዘጋጀው እንዴት ያለ ታላቅ በረከት ነው።»

ይህ ውድ ወንድም ከላይ የተጠቀሰውን ምስክርነት ከሰጠ በኋላ ሰማዕት ሆኗል።

ሃይማኖታዊ ስደት ለክርስቲያኖች ጥልቅ ጭንቀትን ይፈጥራል። ለሕይወታችን ዋስትና ለማግኘት የሕገ መንግሥታዊ መብት ጥያቄ በማንሣት የሚፈጸምብንን በደል ለመቋቋም መሟገት አለብን። ይሁንና ባለሥልጣናቱ ለመተግበር ዳተኞች ሲሆኑና ፈቃደኞች በማይሆኑበት ጊዜ በእርግጥ አማራጭ የሌለው ሁኔታ ይከሰታል። ተፈጥሮአዊ ስሜታችን ኃይልን በኃይል መመለስ ቢሆንም፥ ይህ ግን የመስቀሉ መንገድ አይደለም። ምላሻችን በክርስቶስ ባለን ማንነትና ዘለቄታዊ አባል በሆንንበት መንግሥት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። ጌታ ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት በቀረበበት ወቅት እንዲህ አለ፥ «መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን፥ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር» (ዮሐ. 18:36)። ይህን አመለካከቱን ያረጋገጠው በጌቴሴማኒ በተያዘበት ወቅት ጴጥሮስ ሰይፉን መዝዞ የተሰበሰቡትን ማጥቃት በጀመረበት ጊዜ ነበር። «በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለው:- ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ። ወይስ አባቴን እንድለምን እርሱም አሁን ከአሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይቻል ይመስልሃልን?» (ማቴ. 26:52፥ 53)። በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ክፉት ሲያጋጥመን በሁሉም ላይ ሥልጣን ባለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መታመን ይገባናል።

በቃሉ ውስጥ እንደተጻፈው እግዚአብሔር ለሕይወታችን የሚያዘጋጀው ዕቅድ ለእኛ እጅግ መልካምና የተሻለ መሆኑን ማመን ይኖርብናል። እንዴት መሠቃየት እንዳለብን ለመምረጥ አንችልም። ይሁን እንጂ ጌታ ኢየሱስ ከእኛ ጋር ስለሆነ ሥቃዩን ብቻችንን አንሸከምም። በደማስቆ መንገድ ላይ በሳውል ላይ የተናገራቸውን የሚያጽናኑ ቃላት ተመልከት:- «...፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ?» (ሐዋ. 9:4)።

ምንም ይሁን ምን የእግዚአብሔርን ምርጫ መቀበል አለብን። በዕብራውያን 11፥ በቀደሙት ዘመናት ከእምነት ባሪያዎቹ በአንዳንዶቹ ላይ ስለደረሰው አበሳ አጭር መግለጫ ተሰጥቷል። ይህ በጣም ጠቃሚ ትምህርት ይሰጣል። ከቁ. 33-35 ባለው ዘገባ ላይ በተለይ «... ከሰይፍ ስለት አመለጡ» የሚለውን

አባባል ስንመለከት፡ የድል ማድረግና ነፃ የመውጣት ዘገባ መሆኑን እንገነዘባለን። በአንጻሩ ቁ. 35-38 ያለው የሚያወሳው ጨርሶ የተለየ ታሪክ ነው። «... በሰይፍ ተገድለው ሞቱ» የሚለውን ስናጤን፡ በዚህ ጊዜ ጥፋትና ሞት ሚዛናቸውን ደፍተው እንደነበረ እንረዳለን። በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ዓላማ ውስጥ አንዱ ወገን ሲያመልጥ ሌላው ወገን ይጠፋል። ስለዚህ በሥቃይ የተነሣ ተስፋ አትቁረጥ። ታማኝ አድርጐ እንዲጠብቅህ በመጠየቅና ይህንን በመሳሰሉ ወቅቶች ውስጥ እንዲያሳልፍህ ፊትህን ወደ እርሱ በማንሣት፥ ራስህን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አሳልፈህ ስጥ።

## በእግዚአብሔር ቅጣት ሥርዓት ውስጥ መሠቃየት

ሁኔታችን የፈለገውን ይሁን በእግዚአብሔር እጅ መሠቃየት የእግዚአብሔር ሰዎች ዓለም አቀፋዊ የሆነ ልምምድ ነው። በአጠቃላይ በምዕራብ ያለችው ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር እጅ መሠቃየትን መቀበል እንዳቃታት መናገር አለብኝ። ሀብት፥ ጤንነትና ምቾትን በኃጢአታዊ መንገድ ለማግኘት የምናደርገው ሩጫ እስራኤላውያን በእግዚአብሔር በረከት ከነዓን ሲገቡ ካደረጉት የተሻለ አይደለም። «ይሹሩን (እስራኤል) ወፈረ፥ ረገጠ፤ ወፈረ፥ ደነደነ፥ ሰባ» (ዘዳ. 32፡15)። ይሁንና እግዚአብሔር ለቃሉ ታማኝ ነው። የተቀደሰ ሕይወትን ለመኖር የቆረጡትን ሁሉ በየትኛውም ስፍራ ቢገኙ ከመገሠጽ ወደ ኋላ አይልም።

አንዳንዴ የእግዚአብሔር ተግሣጽ የሚፈጸመው ማስተዋል ከጐደለው ሥራችን የተነሣ ይሆናል፤ አንዳንዴ ደግሞ ከቁጥጥራችን ውጪ ከሆኑ ሁኔታዎች የተነሣ ይሆናል። ሆኖም በምንገሠጽበት ጊዜ ሊኖረን ስለሚገባው ትክክለኛ ዝንባሌ በመጽሐፈ ምሳሌ 3፡11 እና 12 ላይ ተመልክቷል። «... ልጄ ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አትናቅ፥ በገሠጸህም ጊዜ አትመረር። እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥጻልና፥ አባት የሚወድደውን ልጁን እንደሚገሥጽ»። ለምክር ወደ ቃሉ በማዘንበል እርሱ በእኛ ስለሚያከናውናቸው ሁኔታዎች ራሳችንን ከሰጠን የምንጸናበትን ጸጋ ይለግሠናል። እኛም በዚህ ልምምድ ውስጥ እየጠነከርን እንሄዳለን።

ወደ ኋላ መለስ ብዬ በሕይወቴ የሆነውን አንድ ምሳሌ እነሣለሁ። በጣም አስጨናቂ ጊዜ ቢሆንም በውስጡ እንዳድግበት ጌታ ረድቶኛል። የሦስት ዓመት ዕድሜ የነበረው የመጀመሪያ ልጄ በካንሰር በሽታ በአሰቃቂ ሁኔታ ተሠቃይቶ ሲሞት ለመመልከት ተገደድሁ። መጽናኛ የሚሆነኝን ቃል መፈላለጌ ትዝ ይለኛል። መዝሙረ ዳዊት በተለይም (34) አሳረፈኝ። እንደዚሁም ዕብራውያን ምዕራፍ 12 ከቁጥር 5 እስከ 12 ያለው በጣም ረድቶኛል። ይህን ክፍል እንብበው። ይህ የመጽሐፍ ክፍል «የመጽናኛ» ቃል ተብሎ የሚታወቅ መሆኑን

አስተውል (ቁ. 5)። ሌሎች ቁጥሮች ደግሞ እንዲህ ይላሉ፥ «... በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፥ ...» (ቁ. 6)፤ መከራው እንዲደርስብን የተፈቀደው «... ከቅድስናው እንድንካፈል» ነው። (ቁ. 10)፤ ደግሞም «ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል» (ቁ. 11)።

በሁለተኛ ቆሮንቶስ 12:1-10 እንደተዘገበው፥ ሐዋርያው ጳውሎስም በአማኝነቱ በእግዚአብሔር ተግሣጽ ተሠቃይቷል። አስጨናቂው «የሥጋዬ መውጊያ» (ቁ. 7) ያለው የደረሰበት «ወደ ገነት ተነጠቀ» (ቁ. 4) ከሚለው አስደናቂ ነገር በኋላ በመሆኑ ለተለየ ዓላማ እንደነበረ ተረድቷል። ከዚህም በመነሣት «ይኸውም እንዳልታበይ ነው» (ቁ. 7) ሲል ተናግሯል።

ደኅንነት ከዘላለማዊ ሕይወት ማረጋገጫ ባሻገር ሌሎችም ጉልህ አስተዋጽኦዎች እንዳሉት አስተውል። እኛ አሁን የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት ስለሆንን፥ ይህንን አባልነታችንን ጌታ ኢየሱስን በመምሰል እንድናሳይ ይፈልጋል። «እኛም ... የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን» (2ኛ ቆሮ. 3:18)። ይህን ዓይነት መለወጥ እናገኝ ዘንድ እግዚአብሔር ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ የተግሣጽ ሥቃይን በማምጣት ነው።

በእኛ ላይ ስለሚያደርገው ነገር መንገዱ ሙሉ በሙሉ ባይገባንም፥ እንደ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በመላው ሕይወታችን አምላክ እንዲሆን ልንፈቅድለት ይገባል። ይጠብቅህ ዘንድ ኃይሉን አትጠራጠር። እርሱ ሁሉን ቻይ ነው። አሕዛብን በገንቦ እንዳለች ጠብታ ወይም በሚዛን እንዳለ ትንሽ ትቢያ ይቆጥራቸዋል (ኢሳ. 40:15)። ሰዎች በከንቱ ቢማከሩበትም ይሣለቅባቸዋል (መዝሙር. 2)። እርሱን እንድንተማመን ያስፈልጋል። መዝ. (84):5-11 «አቤቱ፥ እርዳታው ከአንተ ዘንድ የሆነለት፥ በልቡም የላይኛውን መንገድ የሚያስብ ሰው ምስጉን ነው። ... ከኃይል ወደ ኃይል ይሄዳሉ፤ የአማልክት አምላክ በጽዮን ይታያል። ... እግዚአብሔር በቅንነት የሚሄዱትን ከመልካም ነገር አያሳጣቸውም» ይላል።

በ1ኛ ጢሞ. 6:19 «እውነተኛውን ሕይወት» ተብሎ በተጠቀሰው የዘላለም ሕይወት ላይ አትኩር። ብፁዕ ጌታችን ኢየሱስን ፊት ለፊት በምናይበት ጊዜ፥ አሁን የምናልፍባቸው ሥቃዮች እስከማይታሰቡ ጠውልገው ይቀራሉ። «ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ» (ሮሜ 8:18) በሚሉት በእነዚህ ቃላት ተጽናና።

## በጥልቀት የሚታሰብ፡

*** በሕይወትህ ለገጠሙህ ፈተናዎችና ሥቃዮች ምላሽህ ምንድን ነው? በሌሎች ጥሩ ክርስቲያኖች ላይ ስለሚደርሰውስ?

*** ጌታ ኢየሱስ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ጠላት በሆነችው ዓለም ውስጥ በሚኖሩ ተከታዮቹ ላይ ይደርስባቸዋል ያለው ምን ነበር?

*** አንድ ሰው «ለምን እግዚአብሔር እኔን ከዚህ ችግር ለመታደግ ኃይሉን አይጠቀምም?» ቢልህ እንዴት ትመልስለታለህ? (ዕብ. 11፡33-38ን ተመልከት።)

*** ከመከራችን ለመማር ፈቃደኞች ከሆንን እግዚአብሔር በሕይወታችን የቁጣ ሥርዓትን እንዴት ነው የሚጠቀምበት?

## አባሪ «መ» «ለአነጋገርህ ጥንቃቄ ይኑርህ?»
## በ. ኤ. ኤች. ዋይትሃውስ

መግቢያ፡- የሚቀጥለው ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ለአንዳንድ ሥነ መለኮታዊ ቃላት ትርጉም ስላላቸው መረዳት ያለውን ልዩነት የሚገልጽ ምንባብ ነው። የተጻፈውም ከባለቤታቸው ጋር በመካከለኛው ምሥራቅ ለሠላሳ ሰባት ዓመታት በሙስሊም ወንጌል ስርጭት ተሰማርተው በነበሩት በሚስተር ኡብሬይ ዋይትሃውስ ነው። እኔም ይህንን ምንባብ እንድጠቀምበት ስለፈቀዱልኝና በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስላሉት ፅንሰ አሳቦችም ስለ አበረከቱልኝ ምክር በጣም አመሰግናቸዋለሁ።

ቃላትን የምንጠቀምባቸው ለእርስ በርስ መግባቢያ ነው። ሁለቱም ወገኖች ተመሳሳይ ቃላት ከተጠቀሙ፥ ብዙ ጊዜ አንዱ የሚናገረው ለሌላው ግልጽ ይሆናል የሚል ግምት ይኖረናል። ነገር ግን ይህ ሁልጊዜ የሚሆን አይደለም። አንድ ቀላል ምሳሌ ተመልከት። አንተ አውስትራሊያዊ ሆነህ ሳለ አሜሪካዊ እንግዳህን በአንድ ታዋቂ ሕንፃ የመጀመሪያ ፎቅ ላይ ልታገኘው ትቀጥረዋለህ እንበል። እዚህ ላይ የሚደንቀው ግን እንግዳህን ለመገናኘት ምንም ዕድል የማይኖርህ መሆኑ ነው። ምክንያቱም፥ አንተ የምታስበው እርሱ ከሚያስበው አራት ሜትር ከፍ ስለሚል ነው። እርሱ አንደኛ ፎቅ የሚለውን አንተ ምድር ቤት ትለዋለህ! እንደዚሁም አንተ አንደኛ ፎቅ የምትለውን እርሱ ሁለተኛ ፎቅ ይለዋል።

እንግዲህ ቀላል በሆነ የፎቅን ደረጃ አስመልክቶ ያንን ያህል አለመግባባት ከተፈጠረ ውስብስብ የሆኑ ሃይማኖታዊ ሥነ-ቃላትን አስመልክቶማ የቱን ያህል የባሰ ይሆናል። ስለዚህ ከሙስሊም ጋር ለመግባባት ከፈለግህ የምትጠቀምባቸው

ቃላት እርሱ የሚያውቃቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ አለብህ። እስኪ ስለ ሃይማኖታዊ ሥነ ቃሎቻችን እናውጠንጥን።

በእርግጥ፥ «በእግዚአብሔር መጀመር» አለብን። ምን ቃል እንጠቀም? ሙስሊም ስለ እግዚአብሔር ሲናገር አላህ እንደሚል እናውቃለን። አላህ እና እግዚአብሔር ማለት አንድ ነውን? ወይስ እርሱ ከእግዚአብሔር ልዩ የሆነ የሙስሊም አምላክ ነው? ለዚህ መልሱ በምትጠቀምበት ቋንቋ ላይ ይወሰናል። የምታነጋግረው በዓረብኛ ከሆነ በእርግጥ «አላህ» በሚለው ቃል ትጠቀማለህ። ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሌላ ዓረብኛ ቃል የለም፤ አላህ የሚለው ቃል የዓረብኛ ቃል እንጂ የሙስሊም ቃል አይደለም። እስልምና ከመምጣቱ ከረጅም ጊዜ በፊት ቃሉ ከሁሉም በላይ መለኮትን ለመግለጽ የሚያገለግል ነበር። ለነገሩ የመሐመድ አባትም አብደላ (አብድ አላህ - የአላህ ባርያ) ይባል ነበር። ዓረብኛ ተናጋሪ አይሁዶች፥ ክርስቲያኖች እና ሙስሊሞች ሁሉ እግዚአብሔር ለማለት የሚጠቀሙት «አላህ»ን ነው።

በሌላ በኩል በአማርኛ የምታነጋግር ከሆንክ የ«አላህ» አቻ ቃል በሆነው በ«እግዚአብሔር» መጠቀም ትችላለህ። ለሙስሊሙ በአማርኛ በምትናገርበት ወቅት፥ ሙስሊሙ ስለ እግዚአብሔር ያለውን መረዳት ለመጥቀስ «እግዚአብሔር» በሚለው ቃል ምትክ «አላህ» በሚለው ብትጠቀም፥ ወይንም እኛ ስለ መለኮት ያለንን መረዳት ለመጥቀስ «እግዚአብሔር» በሚለው ቃል ብትተካው ትርጉም የለሽ ይሆናል። ይህን ዓይነቱ የቃላት አመራረጥ ነገሩን የባሰ ያወሳስብና የጋራ መገናኛ ነጥብን ያሳጣል። እንግዲያው ሙስሊሙ የእምነት አቋሙ የሆነውን «ላ ኢላሃ ኢላ አላህ» እንዴት ነው ወደ አማርኛ ሊተረጎም የሚችለው? መልሱን በአጭር እርሱም ሊተረጉመው አይችልም የሚል ነው። ምክንያቱም የሙስሊም እምነት መገለጽ ያለበት በዓረብኛ በመሆኑ ነው። ነገር ግን እኛ የምንተረጉመው ቢሆን ኖሮ ትክክለኛው የአተረጓጎም ዘዴ «ከእግዚአብሔር በስተቀር ሌላ አምላክ የለም» ማለት ይሆናል።

ይሁን እንጂ አንዱንና ብቸኛውን እግዚአብሔር ለመግለጽ «እግዚአብሔር» («አላህ» በዓረብኛ) በሚል የጋራ ቃል ብንስማማ እንኳ፥ ዳሩ ግን ስለዚህ ስያሜ ይዘት የሚኖረን መረዳት አንድ ነው ወይ? ወይስ እኛም እንደ አሜሪካዊያኖቹና አውስትራሊያውያኖቹ ስለ አንድ ሕንፃ አንደኛ ፎቅ ስንናገር የምንለው የተለያዩ ነገሮችን ይሆናል? ይህ የችግሩ እምብርት ነው። አንድ መለስተኛ መረዳት ያለው ሙስሊም ስለ እግዚአብሔር ሲናገር፥ ከንግግሩ አንድ ነገር ካልጨበጥን በመንመሰክርለት ወቅት ከቶውንም ልንግባባ አንችልም። እጅግ የከበረውን

የወንጌልን ትምህርት ለምን ለጆሮ የሚቀፍና ርኩስ አድርጐ እንደሚቆጥረውም ከቶውንም ልንረዳ አንችልም።

ቁርዓን እግዚአብሔርን አስመልክቶ ያለው ታላቅ ትኩረት፡-

ሀ. አንድ፥ ልዩና ብቸኛ

ለ. ዘላለማዊ

ሐ. ፈጣሪ በመሆኑ ላይ ነው።

ክርስቲያኖች ከላይ ስለ እግዚአብሔር ለተሰጡት አገላለጾች የአመለካከት አንድነታቸውን ቢያሳዩም፥ እንደገና ራሳችንን መጠየቅ ያለብን ለእነዚህ ቃላት የምንሰጠው ይዘት እንደ ሙስሊሞቹ ነው ወይ? የሚለውን ጥያቄ ነው።

በመጀመሪያ ሙስሊሙ እንደሚረዳውና ቁርዓን እንደሚያስተምረው፥ የእግዚአብሔር አንድነት ፍጹም፥ ሁኔታ የማይወስነው አንድነት ያለው ነው። ይህ ደግሞ የቁርዓን ዋነኛ አሳብ ወይም እምብርት ሲሆን፥ ማናቸውም ሙስሊሞች በየጊዜው ጸሎታቸውን በሚደግሙበት ዓይነት በደንብ ተጠቃሎ ቀርቧል። «እርሱ፥ እግዚአብሔር ነው በሉ፥ አንዱና ብቸኛው፤ እግዚአብሔር ዘላለማዊው፥ ፍጹሙ፥ ያልወለደ፥ ያልተወለደ ደግሞም እንደ እርሱ ማንም የለም።»

ስለ እግዚአብሔር በተሰጠ እንዲህ ዓይነት አመለካከት ውስጥ ለእግዚአብሔር «አቻዎች፥ የመለኮት ተጋሪዎች» አሉ ከማለት የከፋ የኃጢአት ቃላት በሙስሊሞች ዓይን አለመኖራቸው ሊያስደንቅ አይገባም። ይህ ይቅርታ የሌለው ኃጢአት ነው፥ «አላህ» በርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም፤ ከዚህ ሌላ ያለውንም (ኃጢአት) ለሻው ሰው ይምራል። በአላህ የሚያጋራ ሰው ታላቅን ኃጢአት በእርግጥ ቀጠፈ» (ቁርዓን 4፡48)። የትኛውም ሙስሊም ጳውሎስ የሚናገርለትን የእግዚአብሔር አንድነት አይቀበልም። «ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን» (1ኛ ቆሮ. 8፡6)። «እግዚአብሔር መንፈስ ነው» (ዮሐ. 4፡24) ከሚለውም ትርጉም ጋር አይስማማም። መናፍስት ፍጡራኖች ተደርገው ከመቆጠራቸውም፥ በተለይም መንፈስ ቅዱስ መልአኩ ገብርኤል ተደርጐ ነው የሚወሰደው።

የእግዚአብሔር አንድነት የሚለው የሙስሊም አስተምህሮት እንደሚያጸናው ከሆነ፥ እግዚአብሔር አንድ፥ ፍጹም፥ ብቸኛና ከሁሉም በላይ በመሆኑ፥ ከእርሱ ጋር የሰውን ልጅ ወይም የመንፈስ ኅብረት የማድረግን አሳብ ከወዲሁ ያገልላል። ለእስላም ሃይማኖት ከፍተኛ ቦታ ያለው መገለጥ እንኳ በሊቀ መላእክት በኩል

ካልሆነ በስተቀር በቀጥታ ሊሆን አይችልም። በእርግጥ የቁርዓኑ እግዚአብሔር ፍጹም የላቀ ስለሆነ፥ ባሕርያቱን አስመልክቶ ምን እንደሚመስል፥ ወይም የእርሱን ማንነት ማሰብ አይቻልም። ወይም ደግሞ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ማድረግ የሚችለውን ነገር ማሰብም፥ መገመትም አይቻልም። በሌላ በኩል፥ በወንጌል እግዚአብሔር ራሱን በክርስቶስ ውስጥ ሲገልጥ፥ በቁርዓን ግን እግዚአብሔር የሚገልጸው ሕጉንና ፈቃዱን ብቻ ነው። እግዚአብሔር ያልታወቀና ሊታወቅ የማይችል፥ የማይደረስበትና የማይመረመር እንደሆነ ለምንጊዜም ይኖራል።

ከእግዚአብሔር አንድነት ቀጥሎ የሚመጣው የእግዚአብሔር ዘላለማዊነት ነው። በቁርዓን ውስጥ ከሚገኙት ታላላቅ ጥቅሶች አንዱ እንዲህ ይላል:- «እግዚአብሔር፥ ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለው፥ ሕያው፥ ዘላለም የሚኖር፥ እንቅልፍ የማይዘውና የማይተኛ፥ በሰማይና በምድር ያሉትን ሁሉ በባለሀብትነት· የሚያስተዳድር ነው። እርሱ ካልፈቀደ ... በስተቀር ለእርሱ የሚማልድ ማነው?» እንዲያውም አንዳንድ የሙስሊም ሥነ - መለኮት አዋቂዎች እግዚአብሔር ዘላለማዊነት እንጂ ሌሎች ባሕርያት የሉትም እስከ ማለትም ይደርሳሉ።

እግዚአብሔር ብቸኛ ከመሆኑና ከዘላለማዊነቱ በመነሣት፥ ፈጣሪ የመሆኑና በፈጣሪነት ሥራውም በሁኔታዎች የማይወሰን የመሆኑ መረዳት ይመነጫል። ሁሉም ነገር ማለትም መልካሙና ክፉው የእግዚአብሔር ገደብ የሌለው የመፍጠር ሥራ ውጤት ነው። ለየትኞቹም የእግዚአብሔር ሥራዎች ሥነ-ምግባራዊ መሠረት የላቸውም። ሁሉም በማይገደብና በማይነገር ፈቃዱ የሚሆን ነው። እንደ ፈቀደ ያደርጋል። የእግዚአብሔርን ሕግጋት በተመለከተ ስለ ሕጎቹ ፍትሐዊነት መናገር መናፍቅነት ነው።

ሁሉም የሙስሊም ሥነ-መለኮታዊ ፅንሰ አሳቦች መተርጐም ያለባቸው ሙስሊሙ ስለ እግዚአብሔር ካለው መረዳት አንጻር መሆን ስላለበት፥ ከእነርሱ አኳያ ሆነን የምንጠቀምባቸውን ሌሎች «የተለመዱ» ቃላት እንመልከት።

1. ኃጢአት:- መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ኃጢአት እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ ዝንባሌ ነው። ከእግዚአብሔር ፈቃድ በተጻራሪ የራሳችንን ፈቃድ መፈጸም ነው። የአዳምና ሔዋን ተወላጆች እንደመሆናችን መጠን፥ ኃጢአተኛ ተፈጥሮ ወርሰናል፤ ስለዚህ በተፈጥሮ መልካም ከማድረግ ይልቅ ክፉ ወደ ማድረጉ እናዘነብላለን።

በተቃራኒ ቁርዓን ሰው ንጹሕ ሁኖ እንደ ተወለደና ፈቃዱን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ማቃረን እንደማይችል ያስተምራል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ፍጹም ነው። ስለዚህ ሰዎችን የሚያስተው እርሱ እንጂ፥ የሰዎች ውስጣዊ ኃጢአተኛ ባሕርይ አይደለም። «አላህ የሻውን ያጠማል፤ የሻውንም ያቀናል፤ እርሱም አሸናፊው ጥበበኛ ነው» (ቁርዓን 14:4)። ስለዚህ ለሙስሊሙ ኃጢአት እግዚአብሔርን ያሳዝነዋል ብሎ ማሰብ አይቻለውም። በተጨማሪ ኃጢአት በዝንባሌነቱ የበደል መሠረተ አሳብ ነው የሚለው ለቁርዓናዊ ትምህርት ባዕድ ነገር ነው። ስለተለዩ ኃጢአቶች (ድርጊቶች) ሲናገር በእግዚአብሔር በተመደበላቸው የከፋት ደረጃ መሠረት ኃጢአቶችን በተለያዩ ክፍሎች ይፈርጃቸዋል።

2. ይህ ደግሞ ንስሐንና ይቅርታን ወደ ማጤኑ ይመራናል። እንደገና ቁርዓን ንስሐን፥ ማለትም አንድ ሰው ስለ ኃጢአቱ የሚያደርገው የንስሐ ዓይነት የሚወሰነው በእግዚአብሔር አነሣሽነትና ቁጥጥር ነው ይላል። ሙስሊም፥ ንስሐ ከኃጢአት ወደ እግዚአብሔር መመለስ መሆኑን ይረዳል፤ ግን እንዲህ ያለውን ድርጊት የሚወስነው እግዚአብሔር ነው ይላል። «አላህ የሻውን ያጠማል፤ የተመለሰውንም ሰው ወደ እርሱ ይመራል በላቸው። . . . አላህ በሻ ኖሮ ሰዎችን በመላ በእርግጥ ይመራቸው እንደ ነበረ አያውቁምን?» (ቁርዓን 13:27-30)። በተለይ በምዕራፍ 28 ቁጥር 67 ላይ ቁርዓን (እግዚአብሔር) ንስሐን አስመልክቶ እንዲህ ይላል:- «የተጸጸተና ያመነ ሰውማ መልካምንም የሠራ ከሚድኑት ሊሆን ይከጅላል። ጌታህም የሚሻውን ይፈጥራል ይመርጣልም ለነሱ (ለሰዎቹ) ምርጫ የላቸውም»።

ይህ እንዲህ ስለሆነ ይቅርታም እንደዚሁ በእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑ የግድ ነው። እንዲያውም ንስሐ መግባት ወይንም አለመግባት ይቅርታ በማስገኘት በኩል አንዳችም ለውጥ አያመጣም። እግዚአብሔር ከወደደ የፈለገውን ይቅር ይላል፤ ካልወደደ ደግሞ ይቅር አይልም። «የሰማያትና የምድር ንግሥታትም የአላህ ነው፤ ለሚሻው ሰው ይምራል፤ የሚሻውንም ይቀጣል፤ አላህም መሐሪ አዛኝም ነው» (ምዕራፍ 48:14)።

3. ይህ ደግሞ ጠለቅ ያለውን የኃጢአት ስርየትና የመቤዠትን ርዕሰ ጉዳይ ያስነሣል። የአብርሃምና የልጁ (በእስልምና እስማኤል ነው) ታሪክ፥ በልጁ ምትክ የአውራ በግ መሥዋዕት መደረግ በቁርዓን (37:99-110) ተዘግቧል። በዚህ ክፍል ውስጥ «በታላቅ መሥዋዕት ተቤዠነው (እስማኤልን)» ተብሏል። በቁርዓን ውስጥ በዚህ ስፍራ ብቻ ነው በመሥዋዕት መቤዠት ለዚያውም ከኃጢአት ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው መቤዠት የተጠቀሰው። ዝም ብሎ ምትክነትን የሚያመለክት ነው። በየዓመቱ ወደ መካ የሚደረገው ሃይማኖታዊ ጉዞ ከተፈጸመ

በኋላ መቤዠቱ ተደረገበት በሚባለው በዚህ ስፍራ ለመታሰቢያነት የእንስሳ መሥዋዕት ይቀርባል።

በቁርዓን «ስርየት» ወይም «መቤዠት» የሚለው ቃል የተጠቀሰባቸው ስድስት ሌሎች ቦታዎች አሉ። በእያንዳንዱ ስፍራ አንድ ሰው ለተፈጸመ ኃጢአት ወይም ላልተከናወነ ግዴታ የሚያደርገውን መተኪያ የሚያሳይ ነው። በአንደኛው ስፍራ (57:15) ላይ በፍርድ ቀን የኃጢአት ማስተሰሪያ (ካሳ) ማቅረብ ጊዜው ያለፈበት እንደሚሆን ይናገራል።

የስርየትና የመቤዠት (ደኅንነት) ጽንሰ አሳብ ለሙስሊም እንግዳ ባይሆንም፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮት ጋር ያለው መመሳሰል በጣም ትንሽ ነው። እንዳውም አንዱ በሌላው ኃጢአተኛ ምትክ የሚፈጸመው መሥዋዕትነት ተቀባይነት የለውም። አንዱ ለሌላው የሚያደርገው መሥዋዕትነት በተለይ በሚቀጥለው የቁርዓን አባባል መሠረት የተከለከለ ነው:- «. . . ነፍስም ሁሉ በራሷ ላይ እንጂ (ክፉን) አትሠራም፤ ተሸካሚም (ነፍስ) የሌላይቱን ሸክም (ኃጢአት) አትሸከምም» (ቁርዓን 6:164)። እንደ ቁርዓን አባባል ከሆነ በእርግጥም ፈጣሪ የፍጥረቱን ኃጢአት ይሸከማል ብሎ መናገር እጅግ የከበደ ስድብ (ጸያፍ ንግግር) ነው።

4. እምነት:- በእስልምና እምነት ማለት ሁልጊዜ የሚያመለክተው በተወሰኑ የእምነት ነጥቦች ላይ የሚደገረውን አእምሮአዊ ስምምነት ሲሆን፥ ይህን የሚያደርግ ሰው እምነቱን በተግባር ቢለማመድም ባይለማመድም አማኝ ይባላል። በልምድ፥ «አማኝ» የሚለው ቃል «ሙስሊም» ለሚለው ተመሳሳይ ነው። አንድ ሙስሊም «በእግዚአብሔር አምናለሁ» በሚልበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት መናገሩ ሳይሆን፥ ነገር ግን ቁርዓን ስለ እርሱ የሚናገረውን መቀበሉን ነው። ይኸውም አንድ ሰው በሰብአዊ መብት ወይም በስበት ሕግ እንደሚያምነው ያክል ማለት ነው። በቁርዓን አመለካከት፥ እንዲህ ዓይነቱ እምነትም እንኳ ቢሆን፥ እንደ ሌሎቹ ሁሉ የሚወሰነው በዘፈቀደና ከተጨባጭ ሁኔታዎች ውጪ በሆነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። «ለማንኛዋም ነፍስ በአላህ ፈቃድ ቢሆን እንጂ ልታምን (ችሎታ) የላትም» (ቁርዓን 10:99)።

ቀደም ብሎ ከተዘረዘሩት ዋቢዎች ለመረዳት እንደሚቻለው ሁለቱ የክርስትና እምነት የጀርባ አጥንት አስተምህሮዎች፥ ማለትም በክርስቶስ እግዚአብሔር ሥጋ መልበሱና ለኃጢአታችን ስርየት በመስቀል ላይ መሞቱ፥ ለሙስሊሞች የተረገሙ (anathema) ቃላት ናቸው። እንዲያውም ቁርዓን ፍጹም ያስተባብላቸዋል። ለክርስቶስ የመለኮትነትን ባሕርይ መስጠት ምሕረት የሌለው ኃጢአት ነው። ለኃጢአት የሚደረግ ማስተሰርያ መሥዋዕት አስፈላጊ አይደለም። ምክንያቱም

እግዚአብሔር የወደደውን ያለ ምንም ሁኔታ ይቅር ስለሚል እና ደግሞም ማንም ሰው ከሥነ-ምግባር ውጭ የሆነውን የአንዱን ሸክም ሌላው መሸከም ስለማይችል ነው። በተጨማሪ እግዚአብሔር ስለ ፍጥረቱ ዘላለማዊ ዕድልና ፈንታ ቅንጣት ታክል የሚጨነቅ አይደለም። «የሚሻውን ሰው ይቀጣል፤ የሚሻውንም ያዝንለታል» (ቁርዓን 29:21)።

እንግዲህ በክርስትናና በእስልምና ተመሣሣይ የሆኑ አባባሎች አንድ ዓይነት ይዘት እንደሌላቸው ማየት ይቻላል። ስለዚህ፥ ለሙስሊሞች የሚመሰክረው ሰው ለእነዚህ አባባሎች በሙስሊሙ የሚሰጡትን የተለያዩ ትርጉሞች የተረዳ ከሆነ፥ ለእነዚህ ቃላት ክርስቲያናዊ ይዘት በመስጠት ሊጠቀምባቸው ይችላል። የጋራ የሆኑ ቃላት ለእምነት መረማመጃዎች እንጂ መሰናከል እንዳይሆኑ በጥንቃቄ ማሰብንና መጸለይን ይጠይቃል።

ማስታወሻ:- ይህን ርእሰ ጉዳይ በስፋት ለመመርመር እስልምናና የእግዚአብሔር ወንጌል «Islam and the Gospel of God, by H Spencer. Delhi, India: ISPCK, 1976.» በሚል ርእስ የተዘጋጀውን መጽሐፍ ተመልከት።

## በጥልቀት የሚታሰብ:

*** ስለ መቤዠት የሙስሊሞች መረዳት ከክርስቲያኖች የሚለየው እንዴት ነው? ለሙስሊሞች ለመመስከር ይህን ልዩነት ማወቅህ ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድን ነው?

*** ሙስሊሞች የእግዚአብሔርን አንድነት የሚገነዘቡት እንዴት ነው? ስለ ሥላሴዎች ያላቸውስ መረዳት ምንድን ነው?

*** ስለ እግዚአብሔር ፈጣሪነት ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ያላቸው መረዳት የሚለያየው እንዴት ነው? ይህስ በምስክርነትህ ላይ ምን ውጤት ያስከትላል?

*** ይህን አባሪ በምዕራፍ 6 ላይ ካለው ሠንጠረዥ ጋር በማጥናት ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ለሥነ መለኮታዊ ቃላት ስለሚሰጡአቸው የተለያዩ ትርጓሜዎች ለመረዳት እንዲጠቅምህ አድርግ።

# አባሪ «ሠ» ወንጌል በደብዳቤ

በከተማ ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ሙስሊሞችን በወንጌል ለመድረስ ቀላሉ ክፍት በር በፖስታ አገልግሎት መጠቀም ነው። የዓለም ሕዝብ በከፍተኛ ሁኔታ ከገጠር ወደ ከተማ በመፍለስ ላይ በመሆኑ፥ ከቀደሙት ዘመናት ይልቅ አሁን የወንጌልን መልእክት በደብዳቤ ማሰራጨት የበለጠ ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል።

ይህ እንዴት እውን ሊሆን እንደሚችል በአንዲት በማውቃት ሴት የተረጋገጠበትን ምሳሌ ቀጥሎ አቅርቤዋለሁ። ጓደኛዬ ብዙ የቱርክ ቤተሰቦች እርሷ ባለችበት አካባቢ ለመኖር እንደመጡ ትረዳለች። ለእነርሱ ወንጌልን ለማድረስ በማሰብ የአካባቢውን ስልክ ቁጥር ማውጫ ትፈልግና የሁሉንም ቱርኮች ስምና አድራሻ ወሰደች ትባላለች። ከዚያም ከቱርክኛ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በማውጣት በእያንዳንዱ አድራሻ አንድ ክፍል ላከች። እንደዚሁ በገበያ ቦታ ካገኘቻቸው ሴቶች ጋር ወዳጅነት ትመሠርትና በየቤታቸው እየሄደች ትጎበኛቸው ጀመር። የአገሯን አኗኗር እንዲለማመዱና የእንግሊዝኛ ቋንቋም እንዲማሩ ረዳቻቸው። ጊዜ ለመውሰድና ጥረት ለማድረግ ፈቃደኛ የሆነ ማንም ሰው፥ ይህን በመሰለ መንገድ ሊሰማራ ይችላል። እንደዚሁም ይህ በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ለተደራጁ ቡድኖችም ማለፍያ ዘዴ ነው።

በአውስትራሊያ ውስጥ 12000 ዓረብኛ ተናጋሪ ቤተሰቦችን የሚደርስ የደብዳቤ ፕሮግራም በሰፊው ተካሂዶ ነበር። በውጤቱም ጠቀም ያሉ ምላሾችን ያስገኘ ነበር። ለዚህም ውጤት ዋነኛው ቁልፍ በፕሮግራሙ የተሳተፉት ከስድስት መቶ የሚበልጡ ክርስቲያኖች ጸሎት ነበር። በኮምፒዩተር ፕሮግራም በተመደበላቸው መሠረት፥ ለእያንዳንዳቸው ለአሥር ሙስሊም ቤተሰቦች በደብዳቤ የሚልኩት የወንጌል ጽሑፍ ተሰጣቸው። ዕቅዱ ክርስቲያኖቹ ለተመደቡላቸው ለአሥሩም የቤተሰብ አባሎች እንዲጸልዩላቸው በእግዚአብሔር ፊት ቃል ኪዳን የሚያስገባ ነበር። ታዲያ አሁንም እንኳን ከእነዚህ ክርስቲያኖች ጋር የጸሎት ደብዳቤዎችን እንለዋወጣለን። ብዙዎቹም በሚልኩልን መልስ «እስከ ዛሬ ድረስ ለቤተሰቦች እየጸለይሁ ነኝ» በማለት ስለሚገልጹልን፥ በጣም ደስ ይለናል።

ከዚህ ዓይነት ሁኔታ በመነሣት፥ ለወንጌል በደብዳቤ ሥርጭት የሚጠቅሙ አንዳንድ ቅድመ ዝግጅቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል:-

1. ከላይ እንደተጠቀሰው የሚጸልዩ ሰዎችን በፕሮግራሙ እንዲሳተፉ በጥሞና መጠየቅ ዋነኛነት አለው። ከዚያም ለእነዚህ የጸሎት ጓዶች ስለ ምላሾችና ስለ ደብዳቤ ክትትል ሁልጊዜ ሊነገራቸው ያስፈልጋል።

2. ከአክራሪ ሙስሊሞች ሊሠነዘርብህ የሚችለውን አደጋ ለማራቅ፥ በተቀባይ አድራሻ ላይ ከፖስታ ሣጥን ቁጥር በቀር የቤት አድራሻህን አትጥቀስ።

3. በምዕራፍ 17 በተጠቀሰው «ነቢያትና ቃሉ» በሚለው መጽሐፍ ዓይነት፥ በባህል ተወዳጅነት ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በሥነ -ጽሑፍ አቀራረብ በማዘጋጀት መጠቀም ያስፈልጋል። ሙስሊሞች ቅዱሳት መጻሕፍትን

ስለሚያከብሩ፥ በዚህ መልክ የተዘጋጀን ቅዱስ ቃል በይበልጥ የማንበብ ዝንባሌ አላቸው።

4. በፖስታ አገልግሎት የመጠቀም ዋናው ጥቅሙ ቅዱሳት መጻሕፍትን በግል ለመቀበል በማስቻሉ ነው። ሙስሊሞች ስለ ወንጌል ያላቸውን ፍላጐት ጓደኞቻቸው ምንም እንዲያውቁባቸው አይፈልጉም። እርስ በርስ ይፈራራሉ። ስለዚህ የምትልከው መልእክት ከውጪም ሲታይ የማይታወቅ መሆኑን አረጋግጥ።

5. በደብዳቤ ከሚላከው ሥነ -ጽሑፍ ጋር ለተከታታይ ትምህርት ሊረዳ የሚችል ሌላም መጽሐፍ መላክ ይቻላል። ለምሳሌ አዲስ ኪዳን፥ የመጽሐፍ ቅዱስ የተልእኮ ኮርስ፥ ወዘተ. ሊሆን ይችላል። የደብዳቤ ፕሮግራም ዓሣን ለማጥመድ መረብን ወደ ባሕር እንደ መጣል ይመስላል። ለወንጌል በትክክል ፍላጐት ያላቸውን ይበልጥ ለመገናኘት ምላሾችን ማግኘት አንዱ መንገድ ነው። ይህ ደግሞ ቀስ በቀስ ወደ ግል ጉብኝትና ምስክርነት ሊመራ ይችላል።

6. የፈለሱ ሰዎችና ስደተኞች በአዲስ አገር ከባድ ችግር ይገጥማቸዋል። ከለመዱት ሰፊ ቤተሰብ የተለዩ ናቸው። ከአዲስ ቋንቋ፥ ካልተለማመዱት ባህልና የአኗኗር ሁኔታ ጋር ትግል ያደርጋሉ። በብቸኝነት፥ ተቀባይነትን በማጣትና ከብካቤን በመነፈግ ስሜት ይዋጣሉ። ከገጠር ወደ ከተማ የሚመጡ ተማሪዎችም ሁኔታ ይህን የመሰለ ነው። በቋንቋቸው የተጻፈ ሥነ -ጽሑፍና ወዳጃዊ ደብዳቤ ማግኘት ያስደስታቸዋል።

7. በከተሞች የሙስሊሞችን ስምና አድራሻዎች የማግኛ ዋነኛ ምንጭ የስልክ ማውጫ ነው። ሙስሊሞች በቀላሉ የሚታወቅ ለየት ያሉ ስሞች አሏቸው። ስሞችን ከስልክ የስምና የአድራሻ መዘርዝር ውስጥ ምልክት እንዲያደርግልህ የሙስሊሞቹ የአገር ተወላጅ የሆነ ሰው ብታገኝ በበለጠ ይረዳሃል።

የደብዳቤ ወንጌል ስርጭት ለረጅም ጊዜ የሚደረግ የጸሎት ውሳኔን ይጠይቃል። ውጤቱን ለመስማት ብትችልም ባትችልም፥ ዳሩ ግን የደብዳቤውን ልውውጥ ማከናወን ያለብህ በእምነትና ጌታ ቃሉን እንደሚጠቀም በመተማመን መሆን አለበት። ተፈላጊው መረቡን አስፍቶ መጣልና ዘሩም መልካም መሬት በማግኘት በብዙ ሙስሊሞች ልብ እንዲወድቅ መጸለይ ነው። ይህን በመሰለ ዕቅድ ውስጥ እግዚአብሔር ቃሉን እንዴት በጸጋ እንደተጠቀመበትና ለሕዝቡም ጸሎት ምላሽ እንደሰጠ ግልጽ የሚያደርገው ዘላለማዊነት ብቻ ይሆናል።

**መልዕክታችሁን በሚከተለው አድራሻ ጻፉልን፡-**

**የሕይወት በር አገልግሎት፥ የፖ.ሣ.ቁጥር 4937፥**

**አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ**